# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 126 ጥር 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# “ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብር ነው”

- የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብር በመሆኑ ለተፈጻሚነቱ ሁሉም በጋራ መቆም እንዳለበት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ /ኢዜማ/ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሙሉአለም ተገኘወርቅ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር በመሆኑ በፓርቲያቸው የሚደገፍ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በርካታ የሕዝብ ቁጥር ይዛ የባህር በር ሳይኖራት መቀጠል ብዙ ጉዳቶች አሉት ያሉት ኃላፊው፣ ስምምነቱ ይህንን ችግር ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

" ከሶማሌላንድ ጋር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# በመዲናዋ ግብር የሚሰውሩ አካላት ላይ ርምጃ ሊወሰድ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ከተማ አስተዳደሩ ግብር የሚሰውሩትን በመለየት ርምጃ ለመውሰድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛና ዝግጁ መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የገቢ አሰባሰቡን ለማሳደግ "ግብር ለሀገር ክብር" በሚል መሪ ሃሳብ የሚያካሂደው የከፍተኛ ግብር ከፋዮች እውቅናና የሽልማት አሰጣጥ መርሀ ግብር በከንቲባ ፅህፈት ቤት ትናንት ተካሂዷል።

በመርሀ ግብሩ ከንቲባ አዳነች እንደተናገሩት፤ ታማኝ ግብር ከፋዮች እንዳሉ ሁሉ ግብር የሚሰውሩም አይጠፉም፡፡ በመሆኑም ያለደረሰኝ ክፍያ የሚፈፅሙ እና ሌብነትና ብልሹ አሰራር ላይ የሚሳተፉ አካላትን በጋራ መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል።

ግብርን መሰወር ከእናት መቀነት እንደመስረቅ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ከተማ አስተዳደሩ ለሕግ ተገዢ ያልሆኑትን ሌቦችና ሕገወጦች በመለየት ርምጃ ለመውሰድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛና ዝግጁ ነው ብለዋል።

ግብርን በወቅቱና በታማኝነት መክፈል ያኮራል፣

በመዲናዋ ግብር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የኑሮ ፈተና ያልበገራቸው እናት

**ተስፋ ፈሩ**

**ሐተታ**

ወይዘሮ ብዙነሽ ጡማ 48 ዓመታቸው ነው፡፡ መሃል ፒያሳ ሲኒማ ኢትዮጵያ አጠገብ የእግረኛ መንገድ ዳር ቆሎ ይሸጣሉ፡፡ የሁለት ወንድና የአንድ ሴት ልጆች እናት ናቸው፡፡ ሦስቱንም ልጆቻቸውን ያሳደጉት አዲስ አበባ ውስጥ አነስተኛ ሥራ በመሥራት የግለሰብ ቤት ተከራይተው እየኖሩ ነው፡፡

"ሥራ ጎበዝ ነኝ፤ መቀመጥ አልወድም፡፡ ያገኘሁትን ሥራ ሳልንቅ እሰራለሁ" የሚሉት እናት ብዙነሽ፣ ቆሎ መሸጥ ከመጀመራቸው በፊት ሻይ እያዞሩ ይሸጡ እንደነበርና በጽዳት ሠራተኝነትም ማገልገላቸውን ይናገራሉ፡፡

ቆሎ ሸጠው በአማካይ በወር እስከ ሦስት ሺህ ብር ያገኛሉ፡፡

የኑሮ ፈተና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









# በመዲናዋ ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

- ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ለአገልግሎቱ ወጪ ተደርጓል

ገጽ 6






# በክልሉ ለአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 300 ሚሊዮን ችግኞች እየተዘጋጁ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ለ2016 የአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር 300 ሚሊዮን ችግኞች እየተዘጋጁ መሆኑን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በ302 ጣቢያዎች ችግኞች እየተዘጋጁ መሆኑም ተገልጿል፡፡

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የተፈጥሮ ሀብትና መሬት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍቅረኢየሱስ አሸናፊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ለ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 300 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ከ300 ሚሊዮን ችግኞች መካከል 180 ሚሊዮን ችግኞች በበልግ የሚተከሉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 120 ሚሊዮን ችግኞች ደግሞ በክረምት ወቅት እንደሚተከሉ አመላክተዋል።

እንደ አቶ ፍቅረኢየሱስ ገለጻ፤ በዘንድሮ የችግኝ መርሀግብር በአጠቃላይ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ እንደሚሳተፍ ይጠበቃል።

የችግኝ ዝግጅቱ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮና በአካባቢ ጥበቃና ደን ልማት ባለሥልጣን እየተከናወነ ይገኛል ያሉት አቶ ፍቅረኢየሱስ፤ ለምግብነት ለሚውሉ የፍራፍሬና የተለያዩ ችግኞች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተዘጋጀ ነው ብለዋል፡፡

የግብርና ደን 119 ሚሊዮን፣ ፍራፍሬ 5 ሚሊዮን፣ ቀርከሀ 14 ሚሊዮን፣ የውበት 5 ሚሊዮን፣ መኖ 11 ሚሊዮን ችግኝ ለማዘጋጀት መታቀዱን የጠቀሱት ኃላፊው፤ አሁን ላይ 126 ሚሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ለችግኝ ተከላው ለአግሮፎረስትሪ ልማት የሚውል ስምንት ሺህ 500 ሄክታር እንዲሁም ለደን ልማት 20 ሺህ 500 ሄክታር በአጠቃላይ 29 ሺህ ሄክታር መሬት መዘጋጀቱን አስረድተዋል፡፡

የሚተከሉት ችግኞች የደን፣ የፍራፍሬና ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው መሆናቸውን ገልጸው፤ ችግኞቹ በ302 ችግኝ ጣቢያዎች ላይ እየተዘጋጁ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ባለፈው ዓመት የክረምት ወቅት ከተተከሉ ችግኞች 85 በመቶ በላይ የሚሆኑት መጽደቃቸውን አስታውቀው፤ ኅብረተሰቡ በችግኝ ተከላ ወቅት ያሳየውን ተሳትፎ በማሳደግ የችግኝ እንክብካቤውን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ እንደሀገር ያስገኛቸውን ጥቅሞችን ጠብቆ ማቆየት እንደሚገባ ገልጸው፤ የአየር ለውጥ የሚያመጣውን ጫና ለመቋቋምና እየተመናመነ የመጣውን የደን ሽፋን ለመመለስ ሁሉም ዜጋ በትብብር ሊሰራ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።



# “ባህላዊ ዕሴቶች ሀገር ጸንታ እንድትቆም ምክንያት ናቸው”

## - አቶ ቀጄላ መርዳሳ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የሚገኙ ባህላዊ ዕሴቶች ሀገር ጸንታ እንድትቆም ምክንያት ሆነዋል ሲሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ ገለጹ።

‹‹ቤተሰብን መመስረት ሀገርን መገንባት ነው›› በሚል መሪ ሃሳብ አንድ ሺህ ጥንዶች የተዳሩበት ሁለተኛው የሺህ ጋብቻ ካርኒቫልና ኤክስፖ ትናንት ተካሂዷል፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ እንደገለጹት፤ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ባህላዊ እሴቶች ሀገር እስከዛሬ ጸንታ እንድትቆም ምክንያት ናቸው፡፡ ከነዚህ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች መካከል ጋብቻ አንዱ ነው፡፡

ማህበረሰብ ያለቤተሰብ ሊቆም አይችልም፤ ትዳር ቤተሰብንና ሀገርን ለማስተዳደር የሚያስችል ኃላፊነት የሚገኝበት በመሆኑ ጥንካሬን መጎናጸፍ የሚቻልበት ነው ብለዋል፡፡

ጋብቻ ቤተሰብንና የሀገራዊ ኃላፊነት ለመቀበል የሚያስችል የሽግግር ጊዜ ነው ያሉት አቶ ቀጄላ፤ ጋብቻ የሀገርንና የማህበረሰብ መሰረት ለማጽናት ጉልህ ድርሻ አለው ብለዋል።

እንደ አቶ ቀጄላ ገለጻ፤ በተለይ እንዲህ በጅማ የሚደረግ ጋብቻ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጎልበት እንዲሁም ባህልን ለማስተዋወቅ ድርሻ አለው፡፡

አቶ ቀጄላ አክለውም፤ በየግል የሚወጣ የተጋነነ ወጪ በመቀነስ ብሎም በቱሪዝም ዘርፍ ገቢ በማስገኘት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

መርሀ- ግብሩ ባህልን ከማጠናከር ጎን ለጎን የቋንቋ እድገትና የተለያዩ እውቀትና ልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚቻልበት እንደሆነም ነው አቶ ቀጄላ የገለጹት፡፡

በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ትዳር ለመመስረት የሚቸገሩ ዜጎች ይኖራሉ ያሉት አቶ ቀጄላ፤ የሺህ ጋብቻ መርሀ- ግብር ይህንን ችግር የሚቀርፍ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ ቀጄላ ገለጻ፤ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት በቅንጅታዊ አሰራር ተጠቃሚ ለመሆንና የጋራ ግብ ለማሳካት ያግዛል፡፡ የሺህ ጋብቻ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በመርሀ ግብሩ ከሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ አንድ ሺህ ጥንዶች በባህላዊ አልባሣት፣ ጌጣጌጦች፣ በባህላዊ ጨዋታዎች፤ ጭፈራዎችና የተለያዩ ትዕይንቶች ደምቀው በጅማ ጋብቻቸውን ፈጽመዋል።

መርሀ ግብሩ በዓለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ ለመመዝገብ የሚችልበት ሁኔታ ለመፍጠር ከሁለት ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ድፎ ዳቦና ከ10 ሺህ በላይ ሲኒዎች በያዘ ረከቦት ቡና የማፍላት ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል።

በተጨማሪም ከ20 ሜትር በላይ ኬክና አንድ ሺህ ሴቶች ቡና የሚያፈሉበት ሥነ ሥርዓት ተካሂዷል።

# በኢኮኖሚ ግንኙነቱ ከገንዘብ ድጋፍ ባሻገር ባለሙያን ማብቃት ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት የሀገሪቱ የኢኮኖሚክ ግንኙነት ከገንዘብ ድጋፍ ባሻገር ባለሙያን ማብቃት ላይ ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ገለጹ፡፡

የፖሊሲ አማካሪ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ሀገሪቱ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር የምታደርገው ግንኙነት ከኢኮኖሚ ባሻገር የሰው ኃይል ኢንቨስትመንት ማሳደግ ላይ ሊያተኩር ይገባል፡፡

በኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲ ረገድ ሙያ ያላቸው አካላት ማሳተፍ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በትብብር ከሚሰጠው የሙያ ስልጠና ጎን ለጎን ጠንካራ የሰው ሀብት አስተዳደር መገንባት እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ እርዳታዎች በሚመጡበት ጊዜ በምን መልኩ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ መነጋገር ተገቢ ነው፡፡ እርዳታ የሚሰጡ አካላት የራሳቸውን ሠራተኞች አምጥተው በራሳቸው ሀገር ደረጃ ደመወዝ የሚከፍሉ ከሆነ የዋጋ ንረቱን ከማባባስ ውጪ ፋይዳ እንደሌለው መክረዋል፡፡

የምጣኔ ሀብትና የፋይናንስ ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጓዙ በበኩላቸው፤ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት ከሀገራት ጋር የሚደረገው የኢኮኖሚ ግንኙነት ከገንዘብ ድጋፍ ባሻገር ባለሙያን ማብቃት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡

አቶ ኃይለመስቀል አክለውም፤ ግንኙነቱ አምራች ኢንዱስትሪን ከማበረታታትና የገበያ ትስስር ከማሳደግ አኳያ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡



ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ(ዶ/ር)



ኃይለመስቀል ጓዙ

ለኢኮኖሚው ማደግ በየዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ በተለይ ልምድ፣ ቴክኖሎጂ ለማምጣት፣ የዶላር እጥረት ችግር ለመቅረፍ፣ የሥራ እድል ለመፍጠር፣የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ለማሳደግ እንዲሁም ለውጭ ሀገር ባለሙያዎች የሚከፈል ክፍያ ለመቀነስ እንደሚያስችል ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ኃይለመስቀል ገለጻ፤ ከሀገራት በስምምነት በስልጠና እንዲሁም በውጪ የትምህርት እድል የሚሄዱ ባለሙያዎች ሀገራቸው ገብተው የሚያገለግሉበት መንገድ መፈጠር አለበት፡፡ ለስልጠና የሚሄዱ ባለሙያዎች በሄዱበት የመቅረት ነገር እንደሚስተዋልም ነው አቶ ኃይለመስቀል የገለጹት፡፡

ጃፓን በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 80 ኢንጅነሮች አውሮፓና አሜሪካ ወስዳ አሰልጥና እንደነበር ያስታወሱት አቶ ኃይለመስቀል፤ የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከሀገራት የኢኮኖሚክ ግንኙነት በማሳደግ በየዘርፉ የባለሙያ ስልጠና ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

አቶ ኃይለመስቀል አክለውም፤ ለስልጠና ወደተለያዩ ሀገራት የሚሄዱ ባለሙያዎች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እንዲያገለግሉ የሚያስችል ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

እንደ አቶ ኃይለመስቀል ገለጻ፤ ለየዘርፉ ባለሙያዎች የሚከፈለው ክፍያ ለሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ከሆነ መልሰው ሀገር ውስጥ ኢንቨስት የሚያደርጉ በመሆኑ ለኢኮኖሚው ማደግ ተጨማሪ ግብዓት ነው፡፡

ዜና

# በመዲናዋ የትራፊክ ፍሰት ማሳለጫና የመንገድ ደህንነት ምልክቶች እየተተከሉ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ 50 የትራፊክ መብራቶች እና አንድ ሺህ የመንገድ ደህንነት ምልክቶች ተከላ እየተከናወነ መሆኑን የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ኤሊያስ ዘርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የትራፊክ ማኔጅመንት ሥራ የትራፊክ እንቅስቃሴውን ከአደጋ ነፃ ማድረግ እና የመንገድ መዘጋጋትን መቀነስ ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሠራ ነው።

በመዲናዋ ያሉት የትራፊክ መብራቶች ውስን በመሆናቸው የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ አደጋ እንዲፈጠር እያደረገ እና የመንገድ መዘጋጋትን እየፈጠረ መሆኑን ጠቅሰው፤ እስከ አሁን በመዲናዋ ያሉት 50 የሚደርሱ ብቻ መሆናቸው ችግሩ እንዲባባስ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

ይህንን ቁጥር ከፍ በማድረግ ችግሮቹን መቅረፍ እንደሚገባ የጠቀሱት ኢንጂነር ኤሊያስ፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት ተጨማሪ 50 የትራፊክ መብራቶች ተከላ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል።



ኢንጂነር ኤሊያስ ዘርጋ

በሩዋንዳ አደባባይ፣ በፒያሳ ደጎል አደባባይ፣ በአራት ኪሎ እና በጎተራ ማሳለጫ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች የትራፊክ መብራቶቹ ተከላ እየተከናወነ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

በተመሳሳይ የመንገድ ላይ ምልክቶቹ መረጃ ሰጪ፣ ክልካይና ተቆጣጣሪ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በተለይ የፍጥነት ወሰንን ጠብቆ ካለማሽከርከር ጋር ተያይዞ የሚከሰት አደጋን ለመከላከል ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው አብራርተዋል።

በመሆኑም ለአሽከርካሪዎች መረጃ የሚሰጡ አንድ ሺህ የሚሆኑ የመንገድ ደህንነት ምልክቶች እየተተከሉ መሆናቸውንም ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ከምህንድስና ሥራዎች ውስጥ በብዛት አደጋ የሚታይባቸው ቦታዎች ላይ የፍጥነት መቀነሻ ጉብታዎች በብዛት እየተሰራ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል ጠጥተው በሚያሽከረክሩ ላይ የተጠናከረ ርምጃ ለመውሰድ የ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በትንፋሽ የአልኮል መጠን መለኪያ መሣሪያ ግዢ መፈፀሙን ገልጸው፤ ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችን ለመለየት የሚደረግ የትንፋሽ ምርመራ አሁን ላይ ባለስልጣኑ የገዛቸውን 75 የአሽከርካሪዎች የትንፋሽ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ለትራፊክ ፖሊሶች ተሰጥቷል ብለዋል።

ባለስልጣኑ በመዲናዋ ነዋሪዎች ላይ ሞት እያደረሰ ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የ13 ዓመታት የመንገድ ደህንነት ስትራቴጂ በመንደፍና ካውንስል በማቋቋም ወደ ትግበራ መግባቱን ጠቅሰው፤ አሁን ላይ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች የዚሁ አካል እንደሆኑ ተናግረዋል።

# የላላ የሕገወጥ አደን ሕግ ወንጀሉ እንዲስፋፋ እያደረገ ነው

## - በአንድ ወር ውስጥ አምስት ዝሆኖች ተገድለዋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ሕገወጥ አደን ላይ የወጣው ሕግ የላላ በመሆኑ ወንጀሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲስፋፋ እያደረገ ነው ሲል የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡ በባቢሌ ፓርክ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አምስት ዝሆኖች በሕገወጦች መገደላቸውም ተነግሯል፡፡

በባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ሕግ ማስከበር ዴስክ ኃላፊ አቶ ዳንኤል አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዱር እንስሳት ሕገወጥ አደንና ዝውውር እንደ ሌሎች የዓለም ሀገራት ኢትዮጵያንም እየፈተናት ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳትን በሕገ ወጥ አደን መግደል በተለያዩ አካባቢዎች እየተፈፀመ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳንኤል፤ በተመሳሳይ እንስሳቱን በቁም በሕገወጥ መንገድ ወደ ሌላ ሀገር ማዘዋወርም የሀገሪቱ ተግዳሮት ነው ብለዋል፡፡

ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመሆን ወንጀለኞችን ተጠያቂ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ዳንኤል፤ ሆኖም በሀገራችን ይህን ሕገወጥ ድርጊት የፈጸሙ ወንጀለኞች የሚቀጡበት የሕግ አግባብ የላላ በመሆኑ ወንጀለኞቹ ድርጊቱን መልሰው የመፈጸም እድላቸው ሰፊ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም ጥብቅ ቦታዎችን እና ብሄራዊ ፓርኮችን ጥሶ በመግባት የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈጸም ከፍተኛ አደጋ ደቅኗል ያሉት ኃላፊው፤ ወደ ጥብቅ ቦታዎች እና ብሔራዊ ፓርኮች በመግባት እርሻ ማረስ፣ ደን መመንጠር፣ ከሰል ማክሰል እና ቤት መስራት በከፍተኛ ሁኔታ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በጥብቅ ቦታዎች ላይ የሚፈጸሙ ሕገወጥ ድርጊቶች እየጨመሩ መምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡



ችግሮቹን ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ጠቅሰውም፤ ተጋላጭ የሆኑ የእንስሳት ዝርያዎች ልየታ ተካሂዷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ዳንኤል ገለፃ፤ በሀገሪቱ ለዚህ ሕገወጥ ተግባር ተጋላጭ ናቸው ተብለው ከተለዩ የዱር እንስሳት መካከል ዝሆን ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡ ፡ በህይወት ከሚነገዱ እንስሳት መካከልም አቦሸማኔ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ችግሩን ለመከላከል ከልየታው በተጨማሪ በዋናነት ህብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሰራ እንደሚገኝም አብራርተዋል፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫውም ህገወጥ የዱር እንስሳት አደንና ዝውውር ምን ያህል ብሄራዊ ጥቅም እንደሚያሳጣ ማሳወቅ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ብለዋል፡፡

በዱር እንስሳት መኖሪያ ስፍራዎች ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶች እንደሌላ ወንጀል ታይተው በቂ ህጋዊ እርምጃ አለመወሰዱ ሕገወጥነቱ እንዲስፋፋ ማድረጉን አብራርተዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለይ ዝሆኖች እየተገደሉ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ዳንኤል፤ በባቢሌ ፓርክ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አምስት ዝሆኖች በህገወጦች ተገድለዋል ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ በጨበራ ጩርጩራ እና በቃፍታ ሽራሮ ቁጥራቸው ብዙ ባይሆንም የዝሆን አደን ተስተውሏል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ይህን ህገወጥነት ለመቀነስ ህጉ ተከልሶ እንዲቀርብ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው ያሉት አቶ ዳንኤል፤ የሚከለሰው ህግም የሌሎች የዓለም ሀገራት ተሞክሮ የተካተተበት እንዲሆን ይሰራል ብለዋል፡፡ የሚከለሰው ህግ ህገወጦችን የሚያስተምር ቅጣት ይዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል ሲሉም አክለዋል፡፡



# አንጋፋው ጋዜጠኛ አስፋው መሸሻ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- አንጋፋው የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢ አስፋው መሸሻ ባደረበት ህመም በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በህክምና ሲታገዝ ቆይቶ ቅዳሜ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

በጋዜጠኝነት ህይወት ላይ በርካታ ዘመናትን ያሳለፈው አስፋው፤ የ97 ነጥብ 1 ኤፍ ኤም አዲስ አይሬ በሚለው ዝግጅት ላይ ብዙዎች ያውቁታል። በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በሚተላለፈው ኑሮ በአሜሪካ በተሰኘው ፕሮግራም የብዙኃንን ቀልብ ስቧል።

እሁድን በኢቢኤስ በተሰኘ የቴሌቪዥን መዝናኛ ዝግጅት በአቅራቢነት ለዓመታት ያገለገለ ሲሆን፤ በበሽታ ተይዞ አልጋ እስኪያዘበት እለት ድረስም በሥራ ገበታው ላይ ይገኝ እንደነበር ተገልጿል።

አስፋው በበጎነት ሥራዎች የሚታወቅ ሲሆን፤ ከአፉ የማይጠፋትን የአባቱ ስጦታ የሆነችውን መኪና ለበጎ አድራጎት ተግባር አውሏል። ከወራት በፊት በመታው ስትሮክ ምክንያት በበሽታው ክብደት ከሀገር ወጥቶ እየታከመም ነበር።

በርካታ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኛ አስፋውን ለማትረፍ የተረባረቡ ሲሆን፤ የድህና ሀብታሙ ኪስ ለአስፋው ተፈትሿል። በዚህም በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር የአሜሪካ ዶላር መሰብሰብ ተችሏል። ሆኖም የአስፋው ህይወት ከዚህ በላይ መሰንበት አልቻለም።

የህይወት ተሞክሮዎቹን ለሕዝብ ባጋራበት ወቅት እንደተናገረው፤ ሁለት የህይወቱን ውድ ሰዎች ማለትም አባቱንና የትዳር አጋሩን በአንድ ቀን ልዩነት አባቱንና ባለቤቱን የተነጠቀበትን ክፉ አጋጣሚ ጠቅሷል። ለእነዚህ ሁለት መራር ዱብዳዎች ሀረር እና አዲስ አበባ ተገኝቶ ሁለቱንም የቀበረበት አጋጣሚ እሱን ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን ያስነባ ነበር።

ሞቅ ደመቅ ሸብረቅ በሚለው ንግግሩ የሚታወቀው አስፋው ላይመለስ ሄዷል። አስፋው ያጋጠመውን ስትሮክ ተከትሎ፣ ለተጨማሪ ህክምና ወደ አሜሪካ በመምጣት፣ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ህክምና ሲደረግለት የቆየ መሆኑ ይታወቃል።

ጋዜጠኛ አስፋው መሸሻ የአንድ ወንድ ልጅ አባት የነበረ ሲሆን፤ በ1959 በአዲስ አበባ ተወልዶ ከትናንት በስቲያ ቅዳሜ ሌሊት 9 ሰዓት ህይወቱ አልፏል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለልጁ ሳምሶን አስፋው (ጃፒ) እንዲሁም ለመላው ቤተሰቡ መፅናናትን ይመኛል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከማዕድኑ ዘርፍ እንደ ሀገር ተጠቃሚ ለመሆን!

በማዕድን ዘርፍ ከፍተኛ ሀብት አላቸው ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ የሆነችው ሀገራችን፤ ከዘርፉ ተገቢውን ጥቅም ማግኘት ሳትችል ቆይታለች። ዘርፉ ከሚፈልገው ከፍተኛ ትኩረት እና ሀብት አንጻር አሁንም ከዘርፉ ተጠቃሚ እየሆነች አይደለችም። ይህንን ሀገራዊ እውነታ የሚቀይር አዲስ ንቅናቄ መፍጠር ካልተቻለ ሁኔታው ባለበት ሊቀጥል ስለመቻሉ ለመገመት የሚከብድ አይደለም ።

ተደጋግሞ እንደሚነገረው ሀገሪቱ ያላትን የማዕድን ሀብት በዓይነትና በመጠን ለይታ አታውቅም ፤ ይህንን ትልቅ ሥራ በኃላፊነት እንደ ሀገር ወስዶ ሊሠራ የሚችል ተቋም (እስከ ሚኒስትር መሥሪያ ቤት ድረስ) በየወቅቱ ቢቋቋምም በአብዛኛው ቢሮክራሲያዊ ከሆነው ሥራ ውጪ በተጨባጭ የሚታይ ውጤት ያስገኘ ሥራ መሥራት ሳይቻል ቀርቷል።

ይህ ደግሞ በተለይ በዘርፉ የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ ለሚደረገው ጥረት ትልቅ ፈተና ሆኗል። ማዕድን ፍለጋም ሆነ ልማት ሊወስድ ከሚችለው ረጅም ጊዜ እና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አንጻር ፤ ባለሀብቱ ወደ ዘርፉ ፈጥኖ እንዳይገባ አድርጎታል። እንደ ሀገር ባለ አቅምም ዘርፉን ለማልማት እንዳይቻል ተግዳሮት ሆኗል።

ከዚህም ባለፈ የሀገሪቱ የማዕድን ዘርፍ ልማት በተወሰኑ ማዕድናት ላይ ትኩረት ማድረጉ ፤ እነሱንም ለማልማት የሚደረገው ጥረት በባህላዊ መንገድ ላይ መመሥረቱ፤ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" በመሆን ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚጠበቀውን ያህል ማበርከት እንዳይችል አድርጎታል።

ከአመራረቱ ባህላዊነት የተነሳ እንደ ወርቅ ያሉ ማዕድናት ለከፍተኛ የኮንትሮባንድ ንግድ ከመጋለጣቸው ባለፈ ፤ የሕገወጥ አልሚዎች ሰለባ ሆነዋል። በዚህ ሕገወጥነት የውጭ ሀገር ዜጎች ሳይቀሩ ተሳታፊ በመሆናቸው ሀገርና ሕዝብን ለከፍተኛ ኪሳራ ተዳርገዋል። ባልተገባ መንገድ የሀገር ሀብት እንዲባክንም ሆኗል።

ለዘርፉ ሁለንተናዊ ዕድገት ሰላም ከሚያበረክተው የማይተካ አስተዋጽኦም አንጻር በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ የሰላም እጦቶች ለዘርፉ ከፍተኛ ፈተና ሆነዋል። በዘርፉ ተንሰራፍቶ ለነበረው ሕገወጥነትም ሆነ የኮንትሮባንድ ንግድ ትልቅ አቅም ሆነዋል።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግሥት ዘርፉን እንደ አንድ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ምሰሶ አድርጎ በመውሰድ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን መሥራት ጀምሯል። ዘርፉ ከነበረበት ውስብስብ ችግሮች አንጻር የሪፎርም ሥራዎቹ የሚጨበጥ ተስፋ ይዘው መምጣት ባይችሉም ፤ በቀጣይ በጠንካራ ዲሲፕሊን ሊመሩ ከቻሉ ተስፋ ሰጪ ስለመሆናቸው መናገር አይከብድም።

ከሁሉም በላይ መንግሥት ዘርፉን እንደ አንድ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ምሰሶ አድርጎ መውሰዱ፤ ትልቅ ሀገራዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይህንን የአስተሳሰብ ለውጥ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት በተለይም የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት በአግባቡ ሊረዱት የሚገባ ነው፤ ለዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ እና እድገትም ወሳኝ ነው።

እነዚህ አካላት ከቀደመው /ከተለማመዱት ቢሮክራሲያዊ ባህል ወጥተው ፤ ዘርፉ ለዕድገቱ የሚፈልገውን የፖሊሲም ሆነ ሌሎች ግብዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመናበብ ፈጥነው ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርም ይጠበቅባቸዋል።

በተለይም ሀገራችን እንደሀገር ለጀመረችው ልማት ስኬታማነት ዘርፉ ከሚኖረው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አንጻር ፤ በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊነታቸው እየጨመሩ የመጡ ማዕድናትን ፤ በሀገር ውስጥ ከማፈላለግ ጀምሮ ተለይተው የታወቁትም ፈጥነው ወደ ልማት የሚገቡበትን መንገድ ማፈላለግ ይኖርባቸዋል።

የውጭ በለሀብቶችን ከመሳብ ጀምሮ ፤ ለማልማት ፈቃደኛ ሆነው የገቡት በተለወዱ የቢሮክራሲ አሰልቺ አሠራሮች እና ገፊ የሕግ ማእቀፎች የማልማት ፍላጎታቸው እንዳይቀዛቀዝ ሕጎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን መከለስ ፤ ማዘመን እና ግልጽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

መላው ሕዝብም እንደ ሀገር የምንፈልገውን ልማት እውን ለማድረግ ፤ የማዕድን ዘርፍ ካለው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አንጻር ፤ ሀገራዊ ሰላምን ለዘለቄታው ለማስፈን በሚደረገው ጥረት በቁርጠኝነት መሳተፍ ፤ በዚህም ሀገራዊ ሰላምን በአስተማማኝ መሠረት ላይ ማነጽ ይኖርበታል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከፍተኛ ትኩረት የሚሻው የጦር መሣሪያ አጠቃቀም ክፍተቶች

ከትዝታ ማስታወሻ

በሀገራችን የጦር መሣሪያ የመያዝ ባህል በብዙ አካባቢዎች የተለመደ ነው። ከዚህም ባለፈ በተለይም በገጠሩ አካባቢ የጦር መሣሪያ ተኩስ ለቅሶ ሆነ ሰርግ ማድመቂያ ጭምር ነው፡፡

ክስተቱ ሁነቱን ላለመደ ሰው ግር ሊያሰኝ ቢችልም፤ ለለመዱት ያደጉበት ለሞተውም ሆነ ለተዳረው ሰው ያላቸውን ክብር ማሳያ ነውና ማንም ለምን? ብሎ ሊጠይቅ አይችልም፡፡

በዚህ ሂደት ወስጥ አልፎ አልፎ የጦር መሣሪያ፤ በአግባቡ የመጠቀም ልምድ በሌላቸው ሰዎች እጅ ይወድቅና፤ ወደሰማይ ለመተኮስ የታሰበችው ጥይት አቅጣጫ ቀይራ ኀዘኑ ላይ ሌላ ኀዘን የተጨመረበት፤ ደስታውም ወደ ኀዘን የተቀየረባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡

የጦር መሣሪያ በቀላሉ በእጅ የመግባቱ እውነታ ሁነቶችን ከማድመቅ ባለፈ ፤ በድሎኛል ዘመዶቼን ጎድቷል ብለው ያሰቡትን ወገን ለመበቀል ያውሉበታል። ከዚህም ባለፈ የወለዱትን ጨቅላ "ደመላሽ" ብሎ ሠይሞ ገና ከምድር ብቅ ከማለቱ የጦር መሣሪያ አጠቃቀም እያሳዩ ማሳደግ ተገቢም ባይሆን የኖርንበት ባህል ነው፡፡

በዚህ ሂደት ጦር መሣሪያን ተጠቅሞ ነፍስ ያጠፋ ግለሰብ ውጤቱን ስለሚያውቀው በሰላም የድሮ መንደሩ ኑሮውን መቀጠል አይታሰብም፡፡ ይልቁንስ ተቅበዝባዥ ሆኖ "ተደረሰብኝ፣ አልተደረሰብኝ፣ የሟች ወገን ተበቀለኝ" በሚል ሰቀቀን ኑሮውን ይገፋል፡፡

በከተማ ያለው የጦር መሣሪያ አጠቃቀም ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ሲጀመር የጦር መሣሪያን ይታጠቁ የነበሩት የሕግ አካላትና በተለያዩ ምክንያት ለደህንነታቸው ስጋት ያለባቸው የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ ነበሩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጦር መሣሪያ መታጠቅ አዲስ ፋሽን ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ ትንሽ ሀብት ያገኘ ሁሉ ከሌላው ዜጋ መለየቱን ለማሳየት ምርጫው ሽጉጥ መታጠቅ መሆኑን መታዘብ ከጀመርን ሰነበትን፡፡

ከፋቱ መሣሪያ መያዝ መምረጣቸው ብቻ ሳይሆን መሣሪያ መያዛቸው እንዲታወቅ የሚያደርጉት የልታይ ልታይ ችግር ነው፡፡ ይሄም አክብሩኝ ፤ አለፍ ሲልም እኔ ያልኩትን ካልሰማችሁ ውጤቱ አደገኛ ነው የሚል መልእክት አዘል እየሆነም ነው፡፡ ይህም ከመልእክት ማስተላለፊያነት ባሻገር በቀላሉ ወደ ሰው ሕይወት መቅጠፊያነት ይሸጋገራል፡፡

በቅርቡ እንኳን በመዲናችን ለትዳር ጥያቄዬ "ተገቢው አዎንታዊ ምላሽ አልተሰጠኝም" ያለ ግለሰብ ለትዳር የፈለጋት ልጅ ላይ በጦር መሣሪያ ጉዳት ማድረሱን ሰምተናል፡፡ የኔ ልትሆን ይገባል፤ ያላትን ሴት በሥራ ቦታዋ ተገኝቶ በስድስት ጥይት መቶ ቤተሰቦቿ በፈጣሪ ተአምር ተረፈች ብለዋል፡፡

የሀገሬ ሰው "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው" እንደሚለው፤ እንኳን ዘመናዊውንና የሰውን ሕይወት ከመኖር ወዳለመኖር ለማሸጋገር ሰከንዶች የሚበቁት የጦር መሣሪያ ይቅርና ባህላዊው ማጭድ እንኳን የከፋው ሰው እጅ ሊገባ አይገባም፡፡ አሁን ግን ለደህንነታችን ስጋት አድሮብናል የሚሉ ጥቂቶች ለብዙሃኑ ደህንነት ስጋት እየሆኑ ነው፡፡

ለዚህ አንድ ማሳያ የሚሆነው በቅርቡ በመዲናችን መሃል ቦሌ የማይተዋወቁ ሰዎች ላይ በተፈጠረ ጊዜያዊ ጸብ በሁለት ጥይት በደቂቃዎች የልጅ አባት የሆነ ግለሰብ ሕይወት ጠፍቷል፡፡ በጊዜያዊ ግጭት በድጋሚ የማይገናኙ፤ ቢገናኙም የማይተዋወቁ ሰዎች ከይቅርታ በማያልፍ ጊዜያዊ ቅሬታ አንዱ ለዘላለም ላይመለስ ሲያሸልብ አንደኛው ቤተሰቡን ትቶ ወደ ማረሚያ ቤት ገብቷል፡፡

በየመጠጥ ቤቱ በሚነሳ ትንንሽ አምባጓሮ ምንም የማይመለከታቸው በመጥፎ ሰዓት በመጥፎ ቦታ የተገኙ ንጹሃን በተባራሪ ጥይት እችን ዓለም እየተሰናበቱ ነው፡፡ ለዚህም በሕጋዊ መልኩ ትክክለኛውን አካል አሳውቀውና የታጠቁት መሣሪያን አስመዝግበው የሚንቀሳቀሱ እንዲሁም በኮንትሮባንድ ሕጋዊ ሒደቱን ሳይከተል መሣሪያ በሚታጠቁ ግለሰቦች ምክንያት ነው፡፡

በጦር መሣሪያ የሰውን ሕይወት ለማጥፋት ወይም አካል ለማጉደል የደቂቃዎች ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ኃይል ያለው መሣሪያ በእጅ ይዞ ነገሮችን በትእግስት ለማሳለፍ ስክነት ይፈልጋል፡፡ ካልሆነ በሀገራችን በጥቂቶች እየታየ

**በተደጋጋሚ ለኔ ልትሆኚ ይገባል፤ የሚላትን ሴት ለማስፈራሪያ አለፍ ሲልም ለማጥቂያነት የሚጠቀሙ ሕዝብ ጠባቂዎችን ታዝበናል**

እንዳለው በግፊያ መሃል ረገጥከኝ፤ እንዲሁም የሚገባኝን ክብር ነፍገኸኛልና መሰል ተራ ምክንያቶች መሣሪያ ለመምዘዝ በቂ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ለደህንነታቸው ያስፈልጋቸዋል ተብሎ መሣሪያ እንዲታጠቁ የሚፈቀድላቸው ግለሰቦች መሣሪያውን መቼና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፤ መሣሪያው እጃቸው ከመግባቱ በፊት በቂ ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ካለበለዚያ ለጥቂቶች ደህንነት ታስቦ የሚሰጣቸው መሣሪያ ብዙሃኑ ላይ አደጋ እንዲያንዣብብ ምክንያት ይሆናል፡፡

በቂ ሥልጠና ከመሰጠቱም ባሻገር ራሳቸውን ለመከላከል ተብሎ የታጠቁት መሣሪያ ዓላማን አለመዘንጋታቸውን በየተወሰነ ጊዜ ማረጋገጥ ያሻል፤ ለዚህም እራሱን የቻለ አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ የብዙሃኑ የደህንነት ስጋት በመቅረፍ ሰላምን እንዲያሰፍኑ የሚታጠቁ የመንግሥት የጸጥታ አካላት ጸጥታን ለማስፈን የታጠቁትን መሣሪያ አጠቃቀም አስመልክቶ፤ በቂ ግንዛቤ እንዲሁም የመሣሪያ አጠቃቀምን አስመልክቶ በቂ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ይህን በበቂ ሁኔታ ማድረግ ሳይቻል በመቆየቱ በቀልድ ብሽሽቅ ወቅት ያልቻላቸውን የሙያ አጋሮቹን መንግሥትና ሕዝብ በአመኔታ ባስታጠቀው መሣሪያ የሚገድል የሕዝብ ጠባቂ ገጥሞናል፡፡ በተደጋጋሚ ለኔ ልትሆኚ ይገባል፤ የሚላትን ሴት ለማስፈራሪያ አለፍ ሲልም ለማጥቂያነት የሚጠቀሙ ሕዝብ ጠባቂዎችን ታዝበናል፡፡

በቅርቡ የተነሳ ግጭትን ለማብረድ ወደሰማይ የተኮሰው ጥይት በአጋጣሚ ሰው ገደለ ሲባል ሰምተናል፡፡ በተመሳሳይ በመዲናችን በመኪናው ውስጥ እያለ ሕይወቱ የጠፋን አሽከርካሪን ነፍስ ያጠፋ ፖሊስ፤ "ለምን?" ተብሎ ሲጠየቅ ጎማውን በመምታት ለማስቆም አስቦ እንደሆነ ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ሃሳቡን አምነን ከተቀበልን ጎማ ለመምታት አነጣጥሮ የተኮሰው ጥይት በመኪናው መስታወት ገብታ አሽከርካሪን ሕይወት የሚቀጥፍ ከሆነ ፖሊሱ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚገባው ልክ አውቆ ወደ ሥራ መግባቱ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ሕዝቡን ጠብቅ ተብሎ ታምኖ መሣሪያ የሚሰጠው አካል ለሕዝብ ስጋት እንዳይሆን በሥነ-ልቦናውም ሆነ በመሣሪያ አጠቃቀም ክህሎቱ ዝግጁነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ በየቦታው የተንሰራፈው ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድና ክምችት የመንግሥትን ትኩረት ይሻል፡፡ በዚህ ረገድ መንግሥት የጀመረው ዘመቻ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሩ ከዚህ የከፋ ደረጃ ሳይደርስ በትጋት መሮጥን ይፈልጋል፡፡

ይህን ማድረግ ስንችል ባደጉት ሀገራት የሚሰማው ግለሰቦች በከፋቸው ቁጥር ወይም የአዕምሮአቸው ጤና በታወከ ቁጥር መሣሪያ ታጥቀው ብዙሃኑ ወደሚገኝበት ቦታ በማቅናት ጥይት በማርከፍከፍ ብሔራዊ ኀዘን ማምጣትን ማስቀረት ይቻላል፡፡ በሀገራችን የሚታየው የጦር መሣሪያ በቀላሉ የማግኘት ጅምር በትኩሱ ሀይ ማለትና ማስቆምን ይሻል፡፡

# በመዲናዋ ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል

## - ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ለአገልግሎቱ ወጪ ተደርጓል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ለአገልግሎቱ ወጪ መደረጉም ተገልጿል፡፡

የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተርና የግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ምነወር ኑረዲን ለኢትየጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኤጀንሲው በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያው በሚገኙ 629 ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ 779 ሺህ 231 ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ምነወር ገለጻ፤ በከተማው በሚገኙ ከቅድመ መደበኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚማሩ 779 ሺህ 231 ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ የምገባ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

የምገባ አገልግሎቱ በዋናነት ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ በአግባቡ ተገኝተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያስችላል ያሉት አቶ ምነወር፤ በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ወላጆች እፎይታ የሚሰጥ ነው ብለዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በትምህርት ዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአገልግሎቱ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉንም ገልጸዋል፡፡

ኤጀንሲው የሚሰጠው ምገባ አገልግሎት ተማሪዎችን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከምገባ ባለፈ የደብተር፣ የተማሪዎች ደንብ ልብስና የመጸዳጃ ቁሳቁሶችን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን አቶ ምነወር አስረድተዋል፡፡

አገልግሎት በሚሰጠባቸው ትምህርት ቤቶች በቂ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የግብዓት ማስቀመጫና የማብሰያ ክፍሎች እንዳላቸው የገለጹት ኃላፊው፤ ጥራቱን የጠበቀና ተመጣጣኝ ምግብ ለተማሪዎች በመቅረብ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ከምገባ አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን የገለጹት አቶ ምነወር፤ የተማሪዎች ምገባን በዘላቂነት በማስቀጠል በአቅም ማነስ የሚፈተኑ ነዋሪዎችን ችግር ለማቃለል በትኩረት ይሰራል ብለዋል፡፡

ለምገባ አገልግሎቱ መሳካት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በመዲናዋ ግብር የሚሰውሩ አካላት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ያስመሰግናል፣ ያሸልማል ብለውም፤ ከግብር ከፋዮች ከሚሰበሰበው ገቢ ሀገራችን ብሎም ከተማችን በሚመጥናት ዕድገትና ብልጽግና ላይ እንድትደርስ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በአጭር የለውጥ ጊዜ ውስጥ ከተማችን እንደ ስሟ ውብ አበባ እና ለነዋሪዎቿ ምቹ ሆና እንድትቀጥል በርካታ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ታማኝ ግብር ከፋዮች የመዲናዋ አሻራዎች በመሆናችሁ ልትኮሩ ይገባል። ታማኝነት ያሸልማል፣ ያኮራል፣ ያስመሰግናል ብለዋል።

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ የከተማ አስተዳደሩን ገፅታ የቀየሩ፣ የሥራ ዕድል የፈጠሩ፣ ኢኮኖሚውን ያነቃቁ ትልልቅ ፕሮጀክቶችና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ የአፍሪካ መዲናነቷን ሊያሳዩ የሚችሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ሥራዎችን መስራት የተቻለው በታማኝ ግብር ከፋዮች ነው።

ከፕሮጀክቶች ባለፈ ምንም ገቢ ለሌላቸው የከተማዋ ነዋሪዎችን በመደገፍ በሰው ተኮር ሥራ ለተሳተፉም በነዋሪዎች ስም ምስጋና አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ በበኩላቸው፤ መድረኩ ሲዘጋጅ ለ5ኛ ጊዜ ሲሆን በዚህም 562 ለሚሆኑ የመዲናዋ ታማኝ ግብር ከፋዮች እውቅናና ሽልማት ይሰጣቸዋል።

ከነዚህ ውስጥ 104 የሚሆኑት ሴት ታማኝ ግብር ከፋዮች ናቸው። 562ቱ ግብር ከፋዮች ተሸላሚ የሆኑት ከሌሎች ግብር ከፋዮች ጋር በ13 ዓይነት መወዳደሪያ መስፈርት ተለይተው ተሸላሚ ሆነዋል ነው ያሉት አቶ አደም።

እንደ አቶ አደም ገለፃ፤ እውቅናው ሌሎች ግብር ከፋዮችን ለማነሳሳት፣ ፍትሐዊ አሰራርን ለማስፈን እና ዘላቂ ፋይናንስ እንዲኖር ያስችላል። በዘንድሮ በጀት ዓመት ከ140 ቢሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ ታቅዷል። ለዚህም የግብር አሰባሰብ ሂደቱን የማሻሻል፣ ሕግ የማስከበር እና ለታማኝ ግብር ከፋዮች እውቅና የመስጠት ሥራ ተሰርቷል።

ለመዲናዋ ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት የግብር ከፋዮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ በ2015 የግብር ዘመን የሚጠበቅባቸውን የግብር ግዴታ በታማኝነትና በወቅቱ ለተወጡ ግብር ከፋዮች ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የፕላቲኒየም፣ የወርቅ እና የብር ደረጃ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።

በመድረኩ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ፣ አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ፣ አትሌት ሰለሞን አረጋ፣ ተማሪ ሊያ ተጋረድ የታክስ አምሳደር ሆነው ተሸልመዋል።

# የኑሮ ፈተና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በመሀል የጽዳት ሥራ በመሥራት በሚያገኙት ተጨማሪ ገቢ ኑሯቸውን ይደጉማሉ። "ሁለት ሺህ ብር የቤት ኪራይ ከፍዬ ሆዴንም እችላለሁ፤ ሳልበላ አላድርም። ቢወደድም ተፍጨርጭሬ ዘይትና ሽንኩርት ያለው ወጥ ሰርቼ እንጀራዬን ጋግሬ በልቼ ነው የምኖረው" ሲሉ በኩራት የሚናገሩት እናት ብዙነሽ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኑሮ እየከበዳቸው መምጣቱን በሀዘኔታ ይገልጻሉ።

እናት ብዙነሽ በጠዋት ተነስተው የቤት ውስጥ ሥራዎችን ካከናወኑ በኋላ ረፋዱ ላይ ቆሎ ይዘው ፒያሳ ይገኛሉ። ሲኒማ ኢትዮጵያ አካባቢ ከመጡ ገና 15 ቀናቸው ነው። ቀደም ብሎ ቆሎ የሚሸጡት አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አካባቢ ነበር። "ደንብ አስከባሪዎች ወጥረው ይዘው አላሰራ አሉኝ። ደሃ ነኝ ይህችን ቆሎ ካልሸጥኩ የምበላውም ሆነ የቤት ኪራይ የምከፍለው የለኝም ስላቸው አልሰማ አሉኝ። በቃ ቦታ ብቀይር ይሻለኛል ብዬ እዚህ መጣሁ" ይላሉ።

እንዲህ ከአንዱ ወደ አንዱ እየተዟዟሩ እየሰሩ ሦስቱንም ልጆቻቸውን እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ አስተምረዋል። ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው በመመረቃቸው እጅግ ደስ እንደሚላቸው የሚናገሩት እናት ብዙነሽ፤ የሴቷ ልጃቸው ትምህርቷን ማቋረጥ ግን የሚያስቆጫቸው ጉዳይ ነው።

አሁን ልጆቻቸው ራሳቸውን ስለቻሉ እናት ብዙነሽ ቤት ተከራይተው የሚኖሩት ብቻቸውን ነው። "ልጆቼ ራሳቸውን ከቻሉ በቂ ነው። በዚህ ዘመን ራስን ችሎ መኖር ትልቅ ነገር ነው። እኔ እነሱን ማስቸገር አልፈልግም" የሚሉት ብርቱዋ ወይዘሮ፤ የቤት ኪራይ ክፍያ ላይ የኑሮ ውድነቱ ተደምሮ ሲያስጨንቃቸውና ሲብስባቸው አንዳንድ ጊዜ ሳይወዱ የልጆቻቸውን እጅ እንደሚያዩ አልሸሸጉም።

ቢሆንላቸውና ቢሞላላቸው ተፍጨርጭረው መኖር እንጂ ፈጽሞ የማንንም እጅ ማየት እንደማይፈልጉ የሚናገሩት እናት ብዙነሽ፤ "እኔ በዚህ ዕድሜዬ መንገድ ዳር ቁጭ ብዬ ቆሎ ስሸጥ በወጣትነትና በጎልማሳነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ጤናማ ሰዎች አጠገቤ ሆነው ሲለምኑ ስመለከት በጣም አዝናለሁ። አዲስ አበባ ውስጥ ሥራ ሳይንቅ በርትቶ ለሚሰራ ሰው ሥራ ሞልቷል። እንዲህ አይነት ሰዎችን ማየት አልፈልግም" ይላሉ።

እናት ብዙነሽን ቀረብ ብሎ ጥቂት ያወራቸው ሰው አንድ ነገረ ይገነዘባል፤ ደስተኛ ናቸው። ቀይ ጸዳል ፊታቸው ላይ የአይን ጥቅሻ ያህል የሚመላለሰው ፈገግታቸው ታክሎበት አንደበት የማይገልጸው ደስታ ይነበብባቸዋል።

በሁኔታቸው ብቻ ሳይሆን በአንደበታቸውም ላገኙት ሰው ደስተኛ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። "እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ። እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፤ ሊያውም ቁጭ ብዬ አይደለም ቆሜ ነው የማመሰግነው" ብለው ከተቀመጡበት ተነስተው ተመልሰው ይቀመጣሉ።

ደግሞ እንደገና ያመሰግናሉ "እግዚአብሔር ሙሉ ጤናዬን ሰጥቶኛል ምንም የከለከለኝ ነገር የለም። ጤንነት የሌለው ሰው ነው መከራና ችግር የሚያየው። ስንቶች የአልጋ ቁራኛ ሆነው አሉ። በጤና ካለሁ ሰርቼ አገኘዋለሁና ዋናው ጤንነቴ ነው። ለእኔ ጤናዬ ከወርቅ ይበልጥብኛል" ብለው ለምስጋና ወደ ሰማይ ይመለከታሉ።

በእስከዛሬው የሥራ ህይወታቸው ያጋጠማቸው ከባድ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ምንድን እንደሆነ ሲገልጹ፤ "በዘመኔ ካለፈው ሁሉ ዛሬ ያለው የኑሮ ውድነት ነው የከበደኝ። የኋላው ጊዜማ አለም ነበረ" ይላሉ።

"ድሮ ብር ባይገኝም ኑሮ እርካሽ ነበር። አሁን ግን ሁሉ ነገር በጣም ውድ ነው። ቀነሰ የሚባል ምንም ነገር የለም፤ ሁሉም ጨመረ ነው የሚባለው" የሚሉት እናት ብዙነሽ፣ ዛሬ አንድ ጉርሻ የማይሞላ ዳቦ አስር ብር እየተገዛ እንዴት ይኖራል ሲሉ ይጠይቃሉ።

# "ከሶማሌላንድ ጋር...

ይህ ደግሞ በዓመት ለወደብ ኪራይ የሚወጣውን ከፍተኛ ገንዘብ በማስቀረት፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ምርትን ወደ ሌሎች ሀገራት ለመላክ ከሚያበረክተው አስተዋጽ አንጻር ትልቅ ጥቅም እንዳለው አመላክተዋል፡፡

የባሕር በር ባለቤት መሆን ከሀገር ደህንነትም አንጻር የሚሰሩ ሥራዎችን ምስጢራዊ ከማድረግ አንጻርም በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አክለው ገልጸዋል፡፡

የተደረገው ስምምነት በድርድር እና በውይይት ተጨማሪ ትብብር እንደሚያመጣ እንዲሁም በምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ የኢኮኖሚ ትብብሮችን ለማድረግ የሚያስችል ዕድሎችን ይዞ መምጣቱንም ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ስምምነት ጋር ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ ስጋቶችና ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ እናምናለን የሚሉት ኃላፊው፤ ስጋቶቹን መዝኖ ውሳኔ ላይ መድረስ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

ብሔራዊ ጥቅም ሲታሰብ የሚሰላው ሌሎችን አለመጉዳት መሆኑን ተናግረው፤ ከአፍሪካ ኅብረት፣ የተባበሩት መንግሥታት እና ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ድርጅቶች ጋር ያለን ግንኙነት በዲፕሎማሲያዊ፣ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ልንደግፈው የሚገባ ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ የምታደርገው ነገር ሌሎች ሀገራትን እስካልጎዳ ድረስ መቀጠል እንዳለበት ተናግረው፤ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር ሌሎች ሀገራት ምን ይሰማቸዋል የሚባለው ነገር መሠረታዊ ጥያቄ እንዳልሆነ አመላክተዋል፡፡

ብሔራዊ ጥቅም ላይ እንደ ሕዝብ አብሮ መቆም ግዴታ መሆኑን አስታውሰው፤ የፖለቲካና የሃሳብ ልዩነቶች ቢኖሩም ብሔራዊ ጥቅም የሚያስገኝ ነገር ላይ ሁሉም በጋራ መቆም እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ምክትል ሊቀመንበር አቶ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ተገቢ እና አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለውጭ ንግድ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ የባሕር በር በጣም ጠቃሚ መሆኑን ተናግረው፤ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ለስምምነቱ ተግባራዊነት አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

ስምምነቱ በኢኮኖሚ እና በዲፕሎማሲው የኢትዮጵያን ገጽታ ከፍ እንደሚያደርግ ተናግረው፤ ኢትዮጵያ እስካሁን ከነበራት የተሻለ ዲፕሎማሲ ልትፈጥር የምትችልበትን አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የተደረገው ስምምነት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅም መሆኑን የጠቆሙት አቶ ቀጄላ፤ ስምምነቱን ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲደግፈው እና ለተፈጻሚነቱ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል መብራቱ አለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የባህር በር ስምምነትን በሚመለከት የጋራ ምክር ቤቱ ጥር 1 ቀን አስቸኳይ ጉባኤ ጠርቶ በጉዳዩ ላይ መምከሩን ገልጸው፤ የተደረገው ስምምነት ለኢትዮጵያ የሚጠቅም በመሆኑ ምክር ቤቱ እንደሚደግፈው ገልጸዋል፡፡ ለአፈጻጸሙም መንግሥት የዲፕሎማሲ ሥራውን ማጠናከር እንዳለበትም አክለው ገልጸዋል። በሀገር ጉዳይ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ መሥራት እንዳለባቸው ተናግረው፤ የባህር በር ለሀገራችን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተፈጻሚነቱ መተባበር አለበት ብለዋል፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ሜካናይዜሽን - የግብርናው እድገት ተስፋ



**ማህሌት አብዱል**

መንግሥት የሀገሪቱን ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የያዘውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማዘመን በርካታ የድጋፍ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: በተለይም የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ አዳዲስ የልማት ስትራቴጂዎችን በመንደፍ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ነው:: ለአብነትም በትንንሽ መሬት ላይ የሚያርሰውን ገበሬ በክላስተር የማደራጀት ሥራ አንዱ ነው። እነዚህ አርሶ አደሮች የተለያዩ የግብርና መሣሪያዎችና ግብዓቶችን በነፃና በአነስተኛ ኪራይ እንዲያገኙ በማድረግ የተጀመሩት የድጋፍ ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት እያመጡ ናቸው::

ከሰሞኑ ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቀው፤ ባለፉት አምስት ወራት ብቻ ግብርናውን ለማዘመን የተጀመረውን ሀገራዊ ጥረት የሚያግዙ ከ919ሺ በላይ የግብርና መካናይዜሽን መሣሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ተደርጓል:: የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በበኩሉ በሀገሪቱ የግብርና እና ማዕድን ዘርፍ ለተሠማሩ ለ39 የሊዝ ፋይናንስ ደንበኞች ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው ማሽኖችን አስረክቧል::

አብዛኛው ገበሬ የሚከተለውን ኋላቀር የግብርና አመራረትና አሠራር ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ለመለወጥና ሀገሪቱ የያዘችውን የልማት ግብ ማሳካት ይቻል ዘንድ በመንግሥት በኩል የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው ምሁራን ይናገራሉ:: በተለይም በምግብ እህል ራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት እውን መሆን የሚችለው በመካናይዜሽን የተመራ ግብርናን ማስፋፋት ሲቻል እንደሆነ አፅዕኖት ሰጥተው ያስገነዝባሉ::

በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሙያ አቶ ወርቃለማው ጣሰው እንደሚሉት፤ አብዛኞቹ በምጣኔ ሀብታቸው ያደጉ ሀገራት ግብርናቸውን በመካናይዜሽንና ቴክኖሎጂ እንዲመራ በማድረጋቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርታማነታቸውን ከፍ አድርገዋል፤ ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን መመገብ ችለዋል:: በአንፃሩ ደግሞ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ሰፊና ለእርሻ የሚሆን መሬትና የአየር ንብረት ቢኖራትም የምትከተለው ኋላቀር፣ በሰው ጉልበት ላይ የተመሠረተ ግብርና በመሆኑ ምርታማነት ማምጣት አልቻለችም። በዚህ ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያለው አርሶ አደር ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ለመኖር ተገዷል::

በሌላ በኩል የሚታረሱትም መሬቶችም ቢሆኑ በአብዛኛው ተራራማና ለመካናይዜሽን እርሻ የማይመቹ በመሆናቸው ጥቂት የማይባለው አርሶአደር ያመረተውን ምርት ከራሱ አልፎ ለገበያ ለማቅረብ ፈተና እንደሚሆንበት ያነሳሉ:: በዚህ ረገድ የየአካባቢውን ሥነ-ምህዳር በጠበቀ መልኩ ዘመናዊ መሣሪያዎች ተጠቅሞ የማረሱም ባህል ‹‹ገና በህፃንነት እድሜ›› ላይ ያለ እንደሆነ ይጠቅሳሉ::

‹‹በእርግጥ በደርግ ዘመነ-መንግሥት ተጀምሮ የነበረው በሰፋፊ እርሻዎች ላይ ሜካናይዝድ በሆኑ ማሽኖች የማረስ ተሞክሮ ትልቅ ተስፋ የነበረው ነበር›› የሚሉት መምህሩ፤ በተለይ አርሲ፤ ባሌና ደቡብ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በህብረት ሥራ ማህበራት አማኝነት ገበሬዎችን በማደራጀት ይከናወን የነበረው የግብርና ሥራ ቀጣይነት ቢኖረው አይደለም ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ጭምር የሚተርፍ እንደነበር ያመለክታሉ::

ይሁንና ከዚያ ወዲህ ጥቂት የሚባሉ የሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች ከሚከናወኑት መካናይዝድ የሆነ ግብርና ውጪ አብዛኛው አርሶአደር የተለመደ የአመራረት ሂደት የሚከተል ከመሆኑም ባሻገር በተበጣጠሰ መሬት ላይ የሚያመርት በመሆኑ ውጤታማነታቸው እምብዛም እንደሆነ ያስረዳሉ:: ‹‹አርሶአደሮቻችን በአብዛኛው ትናንሽ ይዞታ ነው ያላቸው:: እነዚህ ትናንሽ ይዞታዎች ደግሞ ከአዋጭነት፤ ከካፒታል፤ ከእውቀቱም አንፃር መካናይዜሽኑን ለመተግበር ምቹ አይደለም›› ይላሉ::

የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በተለያዩ የግብርና ምርምር ማዕከላትና ተቋማት በኩል የተሠሩት ሥራዎች አመርቂ የሚባሉ እንዳልሆኑ ይናገራሉ:: ‹‹ከዚህ ቀደም አርሶ አደሮቻችን ትላልቅ ማሽኖችን ባይጠቀሙም እንኳን በአነስተኛ ሞተሮች፤ አልያም በእጅ የሚሠሩ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችን ለማምረት ጥረት ስናደርግ ነው የቆየነው:: ይሁንና ብዙ ገፍተው በመሄድ የገበሬዎቻችን ምርታማነት የቀየሩ አይደሉም›› ይላሉ::

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ምህንድስና ዳይሬክተር ዶክተር ላዕከ ከበደ በበኩላቸው እንሚያስረዱት፤ ተቋማቸው ከተሰጠው ተልዕኮዎች መካከል ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅና እንደ የአካባቢ ሁኔታ የማላመድ ሥራ ዋነኞቹ ናቸው:: በተጨማሪም በምርምር ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅና በተወሰነ ደረጃ የማባዛት ሥራ ያከናውናል::

ከዚህ አኳያም ተቋሙ በርካታ ቴክኖሎጂዎችን ማውጣት ቢችልም በሚፈለገው ደረጃ አርሶአደሩ ተደራሽ መሆን አለመቻላቸውን ዳይሬክተሩ ያምናሉ:: ለዚህም አብይ ምክንያቱ የግብርና ምህንድስና ቴክኖሎጂዎች ከፍተኛ ፋይናስ የሚፈልግ መሆኑን አስረድተው፤ ቴክኖሎጂዎቹን የማስተዋወቁ ሥራ ውስንነት እንዳለበት ያመለክታሉ::

‹‹ግብርና ኢንዱስትሪውን ይመግባል፤ ኢንዱስትሪውም ግብርናን:: ለዚህ ደግሞ ኢንዱስትሪዎች ግብርናውን የሚያዘምኑ መሣሪያዎችን ማምረትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል›› በማለት የሚናገሩት ደግሞ አቶ ወርቃለማው ናቸው:: እንደ እሳቸው እምነት፤ አሁን ያሉት ኢንዱስትሪዎች ከግብርናው ግብዓት ቢወስዱም ግብርናውን ለማርካት የሚያስችል ቁመና ላይ አይደሉም:: በተለይም ለግብርና የሚሆኑ ማሽኖችን የማምረት አቅም ባለማጎልበታቸው ዛሬም ድረስ ሀገሪቱ በከፍተኛ ምንዛሬ ከውጭ እያስመጣች ትገኛች:: ዘርፉን ለማሳደግ ከተያዘው የልማት ግብ አኳያ ትራክተር ከውጭ እያስገቡ መገጣጠም ብቻውን ደግሞ አዋጭ አይደለም:: በተለይ አሁን ባለው የውጭ ምንዛሬ እጥረት አኳያ ሌላውንም የልማት ሥራ ወደኋላ ይጎትተዋል::

በሀገሪቱ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ጨርቃ ጨርቅ እያመረቱ ወደ ውጭ መላክ እንጂ በጣም ሰፊ የሆነውን የውስጡን ገበያ ተዳራሽ እንዳላደረጉ የሚናገሩት አቶ ወርቃለማው፤ የውስጡንም ሆነ የውጭውን ገበያ ማዕከል ያደረገ ኢንዱስትሪ መፍጠር ከአጠቃላይ ሀገራዊ እድገት ጋር አብሮ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ሽግግር እንደሚጠይቅ ይገልፃሉ:: ይህ ባለመሆኑ እንደትራክተር የመሳሰሉ ግዙፍ ማሽኖችን የሚያመርቱ ቀርቶ ቀላል ቴክኖሎጂዎችን የሚሠሩ ኢንዱስትሪዎች እንኳን በጣት የሚቆጠሩ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ:: እነዚህም ቢሆኑ በአነስተኛ እርሻዎች ላይ የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን ተደራሽ ማድረግ አለመቻላቸውን ይጠቅሳሉ::

ዶክተር ላዕከ በዚህ ሃሳቡ ይስማማሉ፤ ‹‹አንዱ ያልሠራንበት ዘርፍ ቢኖር ይህ ነው፤ ኢንዱስትሪዎቻችን የሀገር ውስጥ ገበያን ማዕከል ያደረገ ሥራ አይሰሩም›› ይላሉ:: ለዚህ ደግሞ የማምረት አቅሙ ስለሌላቸው ብቻ ሳይሆን ከግብርናው ዘርፍ ጋር ተናቦ የመሥራት ባህሉ ባለመዳበሩ ነው:: ችግሩን ተረድቶ የመፍትሔ አካል የመሆን ተነሳሽነቱ እምብዛም እንደሆነ ያነሳሉ:: በተጨማሪ አብዛኛው አርሶ አደር ከውጭ የሚመጡትን የግብርና መሣሪያዎች የመግዛት አቅም ስለሌለው የግብርና መካናይዜሽን ተጠቃሚ አለመሆኑን ይጠቅሳሉ::

እንደ ዶክተር ላዕከ ሃሳብ ፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት እየተገበረ ያለው የክላስተር እርሻ ሥራ አርሶ አደሩ ተደራጅቶ በዘመናዊ መንገድ እንዲያመርት የሚያደርግ በመሆኑ የሚበረታታ ነው:: በክላስተር መደራጀቱ ትናንሽ መሬት ያላቸውን ከ30 እስከ 200 የሚሆኑ አርሶአደሮች እርሻዎችን በፍላጎት በማቀናጀትና ማሳቸውን በማዋጣት በጋራ ምርታማነታቸውን ለማሳለጥ ያስችላል:: ይህም አርሶ አደሮቹ በፍላጎት ኩታ ገጠም የሆኑ ማሳዎቻቸውን አገናኝተው፤ ትራክተሮችም ሆነ ሌሎች መሣሪያዎችን ገዝተው በጋራ እንዲያመርቱ እድል ይፈጥርላቸዋል::

በተለይም ከአንድ ጥማድ መሬት በላይ ያላቸው ገበሬዎች አብረው እንዲሠሩ ያደርጋል:: ብድር፣ ምርጥ ዘር፣ የማሽን፣ የቴክኒክና ሥልጠና ድጋፍ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል:: በተጨማሪም በተበጣጠሰ መልኩ የሚመረተው ማሳ ወደሰፋ እርሻ በመለወጥ የበለጠ እንዲመረት በማድረግ ዘርፉን ለማሳደግ ያስችላል ተብሎ ይታመናል::

በክላስተር የሚሠሩትም እንኳን ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ተሳስረው የሚሠሩ ቢሆኑም አብዛኞቹ ማሽኖች ጥቂት ሠርተው ሲበላሹ መለዋወጪያ የማይገኝላቸውና የማይጠገኑ በመሆኑ ውጤታማነታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ እንዳለ አቶ ወርቃለማው ያስረዳሉ:: በሌላ በኩል በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገቡም በመሆኑ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየፈተነ ነው ያለው:: በመሆኑም ማሽኖችን በውስጥ አቅም ማጎልበት መቻል ቀዳሚ ተግባር መሆን እንዳለበት ነው የተናገሩት::

በተጨማሪም በዘርፉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂን የሚፈጥር ባለሙያ እንደሀገር እጥረት መኖሩን ይናገራሉ:: ‹‹አብዛኞቹ የቴክኖሎጂ ማዕከላት በቂ የሰው ሃይል የላቸውም፤ ሃረማያ እና ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የመካናይዜሽን ተማሪዎችን በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ያስመርቁ ነበር:: ይሁንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ የመጣ የትምህርት ክፍል ነው:: የተዘጉም ትምህርት ክፍሎች አሉ›› ይላሉ:: በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ብቃት ያለው ባለሙያ የማፍራት ሥራው በጣም የተዳከመ እንደሆነ፤ ይህ በሆነበት ሁኔታ ምርታማትን ማምጣት አዳጋች እንደሆነ ያስረዳሉ::

በሌላ በኩል ግብርና የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ስጋት ያለበት እንደመሆኑ የመንግሥትንም ሆነ የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ድጋፍ ይሻል:: ከዚህ አኳያ መንግሥት የግብርና መሣሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማድረጉ ፋይዳም ዘርፉ ያለበትን ስጋት ለመቅረፍ አንዱ መፍትሄ እንደሆነ ይታመናል:: የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲው አቶ ወርቃለማውም ‹‹በተለይ የእኛ ሀገር ግብርና በተፈጥሮ የሚገኝ ዝናብ ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ሥጋት አለበት:: ይህንን ስጋት ማስወገድ ያስፈልጋል:: ስጋቱን ለማስወገድ ከቀረጥ ነጻ አማራጮች በመስጠት ድጋፎች ማድረግ ይገባል›› ይላሉ::

እነዚህን ማሽኖች ገበሬውም በበድር መልክ እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል እምነት አላቸው:: ‹‹ምክንያቱም ራሳችንን ችለን ማቅረብ እስካልቻልን ድረስ ልማቱንም እውን ማድረግ አስቸጋሪ ነው›› ሲሉ ይናገራሉ:: እነዚህ ሥራዎች በዘመቻ መልክ ከመሥራት ይልቅ፤ ፖሊሲ፤ ተቋምና አደረጃጀት ፈጥሮ መንቀሳቀስ ወሳኝ እንደሆነም ያነሳሉ:: በተለይ አነስተኛ ገበሬውን የሚያሳትፍ አሠራር መዘርጋት ተገቢ እንደሆነም ነው ያስገነዘቡት::

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ የመንግሥት አንዱ ትልቁ ሃላፊነት ፖሊሲ ማውጣት ነው:: እነዚያ ፖሊሲዎች ታች ድረስ የሚተገበሩበትን መመሪያዎችንና ደንቦችን ማዘጋጀት ይጠበቃል:: በዚህ ዘርፍ ያሉትን ምሁራን ዩቨርሲቲዎችንና ማዕከላትን ማደራጀትና ችግሮችን ከስሩ እያረሙ እያስተካከሉ መሄድ ይገባል:: የግብርና ግብዓት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ቀጣይነት ካለው የልማትና የእድገት አቅጣጫ አንፃር በአግባቡ በፖሊሲና በመመሪያ መምራት ይጠይቃል:: በተጨማሪም በሁሉም ዘርፎች በሀገራዊ ስሜት ትስስር መፈጠር አለበት::

በሌላ በኩልም ‹‹ኢንቨስተሮች ዘርፉ ከእጅ ወደአፍ ከምንለው ሥርዓት ወደ ገበያ መር ግብርና መሸጋገር አለበት:: ለዚህም ገበያን ትኩረት አድርጎ ማምረት ይፈልጋል›› የሚሉት መምህሩ፤ አዋጭና ምርታማ ለመሆኑን መሬትን፤ ከሥነ ምህዳሩ እንዲሁም ከየአካባቢው የአየር ንብረት አስማምቶ መሥራት የሚያስችል ቴክኖሎጂንና የአሠራ ሥርዓትን መጠቀም ወሳኝ መሆኑም ነው ያስገነዘቡት:: አነስተኛ ገበሬውም ብዙ አይነት አዝዕርቶችን ከመዝራት አዋጭ የሆኑ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚፈልገውን ደግሞ ከገበያ መግዛት መቻል አለበት:: ለዚህም የገበሬውን ግንዛቤ የሚያሳድጉ ሥልጠናዎች መስጠት እንደሚገባ ይናገራሉ::

የእሴት ሰንሰለት የመፍጠር ሥራውም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አቶ ወርቃለማው አመልክተው፤ ‹‹የምርምር ማዕከላት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ፤ የግል አምራቾችና ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የየራሳቸውን ድርሻ ከተወጡ ግብርናው እየነቃና እየተሻሻለ ይሄዳል›› በማለት ተናግረዋል::

ዶክተር ላዕከ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ቴክኖሎጂዎችን ለመግዛት አርሶአደሩ የግንዛቤ እጥረት ብቻ ሳይሆን የፋይናንስ አቅም የለውም:: በመሆኑም ከግንዛቤ ማስጨበጡ ጎን ለጎን በረጅም ጊዜና በአነስተኛ ብድር ማሽኖቹን የሚያገኝበት ሁኔታ ሊፈጠርለት ይገባል:: አሁን የተጀመረው ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማድረጉም ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት:: በተጨማሪም ማዕከሉ የሚያወጣቸውን ቴክኖሎጂዎች በስፋት የሚያባዙ አካላትም ሊበረታቱ ይገባል:: ከዚሁ ጎን ለጎን በቂና መሣያዎቹን ማንቀሳቀስ የሚችል የሰው ሃይል አብሮ በማብቃት አገልገሎቱን መስጠትና መዘጋጀት ይጠይቃል::

እንደምሁራኑ እምነት፤ ሀገሪቱ በቂና ያልታረሰ መሬት፤ የከርሰ ምድር ውሃ፤ በርካታ ወንዞችና ጅረቶች ባለቤት እንደመሆንዋ እየተከተለች ያለችውን ኋላቀር የግብርና ሥርዓት ካዘመነች በተለይ የምርት ሂደቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ ከቻለች ፤ ከሁሉም በላይ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ሰላም ከሰፈነ ምኞት ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ወደ መካከለኛ ኢኮኖሚ የማደግ ተስፋዋን እውን ማድረግ ትችላለች:: በአግባቡ በእቅድ የተመራ ሥራ ከተሠራና በቂ ጥረት ከተረደረገ ራሷን መመገብ ብቻ ሳይሆን ለብዙ የጎረቤት ሀገሮች ምርቶቿን ማቅረብ የሚያስችል አቅም ትፈጥራለች::

ማህበራዊ
# አስኳላ

## “የመጻሕፍት ዛፍ” በአብርኆት ቤተ-መጻሕፍት

ግርማ መንግሥቴ



መጻሕፍት እና አንባቢ(ያን) ተለያይተው የሚታዩ ጉዳዮች አይደሉም። ተጠራሪ ናቸው። እንደውም፣ “ጸሐፊ”ን ጨምሮ ሶስቱም አንድም ሶስትም ናቸው። በመሆኑም፣ ስለ አንዱ ስናወራ ሌላኛውን መንካታችን፤ ስለ አንደኛው ስናነሳ ስለ ሌላኛው ማውጋታችን ወዘተ የግድ ይሆናል ማለት ነው - ጋብቻቸው የዋዛ ባለ መሆኑ።

ከ240 ሺህ በላይ መጻሕፍትና 300 ሺህ ጥናታዊ ጽሑፎችን ስለ ያዘው፤ ስለ ዘመናዊው አብርኆት ቤተ-መጻሕፍት ሲነሳ ስለ መጻሕፍት፣ ስለ መጻሕፍት ሲነሳ ስለ አንባቢ(ያን)፣ ስለ አንባቢ(ያን) ሲነሳ ስለ ንባብ (ባህል) ወዘተ መነሳቱ የግድ መሆኑን ነው የላይኛው መግቢያ አንቀፅ የሚናገረው። ይህንን ስንል ጉዳዩን “በጠባብ ሰርክል ተነጋገሩበት” እንዲሉ አንዳንድ ሰብሳቢያን ሆኖብን እንጂ የቤተ-መጻሕፍት ጉዳይ ሲናሳ አብረው ሊነሱ የሚገባቸው መሠረታውያን እነዚህ ብቻ ሆነው አይደለም፤ በርካቶች አሉ።

ርእሳችንን ጠበቅ አድርገን ውይይታችንን እንቀጥል ዘንድ ርእሰ ጉዳያችን ግድ ይለናልና ወደ እዛው እንሂድ።

ሰሞኑን የእኛም፣ የነጮቹም (የእነሱ ገናን የታከከ የአዲስ አመት መግቢያን ጨምሮ) የገና በዓል ተከብሮ ማለፉ ይታወሳል፤ ስለ መታወሱ ማስረጃው ደግሞ አሁንም ድረስ የበዓሉ ልዩ ልዩ ገፅታዎች እየታዩ መሆናቸው ሲሆን፣ አንዱም አልባሳት ናቸው። እየተነጋገርንበት ያለውና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የመልእክቱ አጋዥ የሆነው ፎቶግራፍ ላይ የሚታየውም (በ“ክሪስማስ ትሪ” ፋንታ የቆመው የመጻሕፍት ዛፍ) እስካሁን አለመፍረሱም እንደዛው።

ከሁሉም በፊት፣ ገና ወረቱ አልወጣልንምና፣ ፍቅራችን አልሰከነምና . . . ስለ ግዙፍና ዘመናዊው፣ ባለ ግርማ ሞገሱ፣ ሁሉን አቀፉ፣ ሰብሳቢና አሰባሳቢው፣ ውብና ማራኪው፣ በፀአዳ ሥፍራ ላይ ስላረፈውና በመሀል አዲስ አበባ መልህቁን በመጣል አራት ኪሎ ላይ እየተገማሸረ ስላለው፤ ከ1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ስለ ተገነባው አብርኆት ቤተ-መጻሕፍት ተግባራትና መገለጫዎቹን ጥቂት እንበል።

እጅግ የተመረጡ የተፈጥሮ ሳይንስና የማኅበራዊ ሳይንስ፣ የቋንቋና የሥነ-ጥበብ መጻሕፍትንና ሌሎች በርካቶችን ለያዘው፤ የተለያዩ አንባቢዎችን ፍላጎት በማርካት ላይ ለሚገኘው ቤተ-መጻሕፍት ባደረጉት የዲጂታላይዜሽን መተግበር አስተዋፅኦ ከራሺያው HSE University የዲፕሎማ ሽልማት እና እውቅና በተሰጣቸው፤ የe-governance እና ዲጂታላይዜሽን ተሸላሚ በሆኑት፣ በዋና ዳይሬክተሩ ኢንጅነር ውብአየሁ ማሞ፤ እንዲሁም ከዛ በፊትና በኋላ በተለያዩ ምንጮች አማካኝነት ለሕዝብ በተለቀቁ መረጃዎች ላይ ይፋ እንደተደረገው፣ አብርኆት ቤተ-መጻሕፍት፡-

- የአገልግሎት አድማሱን እያሰፋ ዛሬ በቀን እስከ 15 ሺህ አንባቢያን (የሀገር ውስጥም የውጭ ሀገር ዜጎችም) የሚስተናገዱበት ተቋም ሆኗል፤
- ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት፣ ማለትም ከታህሳስ 24/2014 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ እስከ ህዳር 17/2016 ዓ.ም ከ10 ሚሊዮን በላይ አንባቢያንንና የጥናትና ምርምር ባለሙያዎችን አስተናግዷል፤
- በ4 ወለሎቹ 1.4 ሚሊዮን መጻሕፍትን መያዝ የሚችል፣ 1.5 ኪ.ሜ መደርደሪያ ያለው፤ በአንድ ጊዜ 115 ተሽከርካሪዎችን ለማቆም የሚያስችል የተሟላ የመኪና ማቆሚያ ያለው አብርኆት በእድሜ ደረጃ ለሕጻናት፣ ለታዳጊዎች፣ ለወጣቶች፣ ለጎልማሶችና ለሽማግሌዎች የሚሆኑ ይዘቶች ያሏቸው መጻሕፍት ያሉት፣ ሁሉንም ዜጎች ታሳቢ ያደረገ የመረጃ ምንጭ ክምችትን ይዟል፤
- “ቤተ መጻሕፍቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና የሚያምር የኪነ-ሕንጻ ጥበብ ያረፈበት ነው” የተባለለት ሁለ-ገብ ቤተመጻሕፍት የዜጎችን የማንበብ ባህል ለማዳበር ትልቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፣
- በአንድ ጊዜ ከ2 ሺህ በላይ ተጠቃሚዎችን ማስተናገድ የሚችለው ቤተ መጻሕፍት በውስጡ ከማንበቢያ ስፍራ በተጨማሪ የስብሰባ አዳራሽ፣ ካፍቴሪያ፣ የህፃናትና የአጥቢ እናቶች ማንበቢያ ሥፍራዎችን፤ የግል፣ የቡድን ወዘተ ማጥኛ ሥፍራዎችን አካትቶ የያዘ ግዙፍ ተቋም ነው።

በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ ከሆኑ 10 ቤተ-መጻሕፍት መካከል አንዱ የሆነውና በ19 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው አብርሆት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማርካት ከህዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የ24 ሰዓት ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠቱ፤ እንዲሁም፣ የንባብ አገልግሎት መስጠት በጀመረበት ጊዜ ከጠዋቱ 2፡00 ተከፍቶ እስከ ምሽት 12፡00 ድረስ ለንባብ ክፍት ሆኖ እስከ ህዳር 13/2015 ዓ.ም ድረስ ያገለግል የነበረ ሲሆን፤ በተደጋጋሚ በሚያቀርበው የተጠቃሚዎች ጥያቄ መሰረትና የአገልግሎት ፈላጊው ቁጥር እየጨመረ ስለመጣ ከህዳር 14/2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ድረስ ማስተናገድ መጀመሩ የአብርኆት ቤተ-መጻሕፍት የተግባር ኩራት ናቸው።



እነዚህ ብቻ አይደሉም የአብርኆት መለያዎች፤ ቤተመጻሕፍቱ ሌሎችም ወቅታዊ የሆኑ ልዩ መለያዎች ያሉት ሲሆን፡-

- ወደ ሥራ በገባ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥራቱንና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት በመቻሉ የሲልክ ሮድ ቤተመጻሕፍት ጥራት ጥምረት (SRILA)ን መቀላቀሉ፤
- የመገኛ ሥፍራው ማእከላዊነት፣ የደኅንነት ዋስትና ያለው መሆኑ፣ ንጽሕናውና ምቹ ከባቢን በመጎናፀፉ ምክንያት ተመራጭ መሆኑ፤
- ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ያካተተ የቴክኖሎጂ እና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ሥልጠናን መስጠቱ (የ5ኛው ዙር ሠልጣኞች ተመርቀዋል)፤
- ከተለያዩ አካላት (ለምሳሌ ከስፔን ኤምባሲ) ጋር በመሆን ለህፃናት የሚሆኑ አዝናኝ እና ትምህርታዊ የአሻንጉሊት ትርኢት ማካሄዱ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አገልግሎት ለሚሰጡ ከ100 በላይ የቤተ-መጻሕፍት ባለሙያዎች የመጀመሪያ ዙር ሥልጠና መስጠቱና የመዲናዋን የቤተ-መጻሕፍት አቅም የሚያሳድጉ ተግባራትን በማከናወን ላይ መገኘቱ፤
- የዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀንን “አብርሆት ለልበ ብርሀኖች” በሚል መሪ ቃል በቤተ-መጻሕፍቱ በፓናል ውይይት ማክበሩ፤

እና ሌሎች ተግባራቱ ከቤተ-መጻሕፍት ሁሉ ፊት መሪ ያደርጉታልና “እሰየው” ስንል ከውስጣችን፤ “አለ ገና”ንም ስናከልበት ከልባችን ነው።

የ24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው፤ ከተገነባ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ጥራትና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የቻለ መሆኑ መቀመጫውን ቻይና ያደረገው የሲልክ ሮድ ዓለም አቀፍ የቤተመጻሕፍት ጥምረት ለዓለም ይፋ ያደረገለት፤ ተቋሙ የኢትዮጵያ ቤተ-መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን የደመቀ የእውቀት መዳረሻ ቦታ መሆኑ፣ ይህም 43ኛ ቤተመጻሕፍ ተቋማት ጥምረት ሆኖ መመዝገብ ያስቻለው መሆኑ በዚሁ ተቋም (SRILA) የተነገረለት አብርኆት ቤተ-መጻሕፍቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት (ገና)ን ምክንያት በማድረግ ማዕድ ያጋራ ሲሆን፤ ማዕድ ማጋራት የተደረገላቸው በከተማው የሚገኙ አቅመ ደካሞችና የጎዳና ተዳዳሪዎች ናቸው። በማዕድ ማጋራቱ መርሃ-ግብር ላይ የተገኙት የአብርኆት ቤተመጻሕፍት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ውባየው እንደገለፁት (በቤተ መጻሕፍቱ የቴሌግራም ገፅ ላይ ሰፍሮ እንደሚነበበውም) ማንኛችንም ብንሆን መሰል በዓላትን ስናከብር አንዱ ለሌላው ያለውን በማካፈልና በልግስና ሊሆን ይገባል።

የአብርሆት ቤተመጻሕፍት አስገራሚ ግንባታና አቀማመጥ፣ እንዲሁም ዙሪያ ጊቢው የተላበሰው አረንጓዴያማ ገፅታ የተቋሙን ሞገስ ከፍ ከማድረጉም በላይ የዜጎች የንባብ ፍላጎት ይቀሰቀስ ዘንድ የሚጋብዝ መሆኑ፤ በአሁኑ ጊዜ ከሶስት መቶ ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ የጥናትና ምርምር ውጤቶች፣ ከመቶ ሃያ ሺህ በላይ ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን የያዘ ከመሆኑም ባሻገር፤ በውስጡ ከአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ መጻሕፍትን መያዙ በSRILA የተመሰከረለት አብርኆት ቤተመጻሕፍት፤ የትምህርት ተቋማት የዜጎች መብቀያዎች፣ ለነገ ሀገር ተረካቢዎች መገኛዎች መሆናቸውን፣ አውቀትን አላምጦ ለመዋጥ ደግሞ የቤተ መጻሕፍቶች ሚና የጎላ መሆኑን ደጋግመው በሚናገሩ ወገኖች ዘንድ አብርኆት ሳይጠቀስ የማይታለፍ ተቋም ነው።

ከዓለም አቀፍ የዘርፉ ተቋማት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቤተ መጻሕፍትን (በዋናነት የዲጂታል አገልግሎት አሰጣጥን) አገልግሎት የሚያሳድጉ ተግባራት እያከናወነ መገኘቱ፤ ከስፔኑ ሮያል ላይብረሪ፣ ከማድሪድ ኮምፕሊተንስ ዩኒቨርሲቲ የቤተ መጻሕፍት፣ ከበርክሌይ ዩኒቨርሲቲና ከኮንግረስ ላይብረሪ ጋር በመተባበር በዲጂታል ዘርፉ ሥልጠና የመስጠት፣ መሠረተ ልማት የማሟላት እና ሌሎች የድጋፍ ተግባራትን ቤተ-መጻሕፍቱ እያከናወነ መገኘቱ ወዘተርፈ ከሌሎች የሀገራችን ቤተ-መጻሕፍት ለየት የሚያደርጉት ተግባራቱ ሊያስመሰግኑት ብቻ ሳይሆን፤ ለሌሎችም በአርአያነት የሚተርፉ ናቸውና “ከአብርኆት ጋር ወደ ፊት!!!” ማለት የግድ ይሆናል።

“በብዙ ቦታዎችና ጉባዔዎች፣ በመደበኛም ሆነ በኢ-መደበኛ ውይይቶች አንባቢ ጠፋ፣ የንባብ ባህል ወደቀ ሲባል ተደጋግሞ ይሰማል፡፡ እርግጥ ነው፤ የንባብ ልምድ ቀንሶ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ለንባብ ማሳለጫና ማበረታቻ የሚሆን ምን የተመቻቸ ነገር አለና ነው ትውልዱ በንባብ ጠልነት የሚከሰሰው? አሁን ትልቁ ችግር የሚያነብ ሰው እጥረት ሳሆን የሚያነቡበት ቦታ (አብያተ-መጻሕፍት) መጥፋት ነው፡፡” የሚለውን ያረጋገጠ፤ የከተማው (አአ) መስተዳድር “ቁጥር 2 አብርኆት ቤተመጻሕፍት”ን በሌላ የከተማዋ ስፍራ ላይ ለመገንባት ሙሉ ስራውን አጠናቆ ወደ ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኝ ዘንድ ገፋፊ ምክንያት መሆኑ አብርኆት ቤተመጻሕፍትን ለማድነቅ ሌላውና ተጨማሪው ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ፣ አብርኆት ቤተመጻሕፍት እንደ ስሙ አይደለም ማለት የሚቻል አይደለም። ወደ ተሻለ ነገ እየገሰገሰ በመሆኑም ሆነ በፈር ቀዳጅነቱም የሚታማ አለመሆኑን ከላይ በጥቂቱ የተዘረዘሩት የተለያዩ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ገጽታዎቹ ማሳያዎች ናቸውና ድንቅ ነው። የአንባቢያንን ጥም በመቁረጥም በኩል (ይህ ጸሐፊ ራሱ ምስክር ነውና) ተሳክቶለታል። የወደፊት ማንነቱን የዛሬው ሁኔታውና ይዞታው አመላካች ነውና ከሀገርና አህጉርም ባለፈ ለዓለም ኩራት ሊሆን ስለ መቻሉ አለመናገር ንፍገት ይሆናል። ከእድሜው በላይ፣ እጅግ ከእድሜው በላይ የሠራና እየሠራ ያለ ዘመናዊ ተቋም መሆኑንም አለመመስከርም መረገም ነው። ገና በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን እንደሚያገኝ ከወዲሁ መናገር ነቢይ አያስብልምና እዚህ ጋ ማንሳቱ የግድ ይሆናል። “ኋላ የመጣ አይን አወጣ” ካልተባለ በስተቀር፣ ነገ እነ ኮንግረስ ቤተ-መጻሕፍትን ወደ ታች ላለማየቱ ዋስትና የለምና ከወዲሁ “ይበል”፣ “ይሁን”፣ “ያድርገው” ማለት ተገቢ ይሆናል።

የማጠቃለያው ማጠቃለያ፣ ኢትዮጵያ አንድ ርምጃ ወደ ፊት ተራምዳለች ከተባለ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት የሆነው አብርኆት አንዱ ማሳያ አይደለም ማለት አይቻልምና “ነው!!!” ብሎ ማፅደቅ የግድ ይሆናል። ሌሎች ተቋማትም ይህንኑ አርአያነት ይከተሉት ዘንድ ማሳሰብ ሃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ትክክል ነውና አድርገነዋል። የአንባቢያን (ተጠቃሚዎች) ሥነሥርዓትም ምስጋና ሳይቸረው የሚታለፍ አይደለም “ይቀጥል!!!” ስንል ከምስጋና ጋር ነው። በተለይ፣ ዛፍ ከመቁረጥ ታቅቦ፣ የመጻሕፍት ዛፍን በመሥራት ገናን ማክበሩ ለብዙዎቻችን ተምሳሌት ከመሆንም ባለፈ በየቤትና ተቋሞቻችን በመጻሕፍት ዛፍ ገናን እናከብር ዘንድ ያበረታታልና ለዛ ያበቃን ዘንድ ስንመኝ እኛም በመጽሐፍ “ቺርስ!!!” በማለት ነው። ቺርስ!!!

# ወቅታዊ

## ‹‹ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ተቀዛቅዞ የነበረውን ዲፕሎማሲ በአስተማማኝ መልኩ መመለስ ተችሏል ››

- አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ-የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ



ስምስም መንግሥቱ

ኢትዮጵያ በፖለቲካው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፣ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲም ከዓለም ሀገራት ጋር በምታደርገው የሁለትዮሽ ግንኙነቶች የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ የንግድ ልውውጦችን በማጠናከር ፣ በሀገሯ ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ሌላው ዓለም እንዲያውቀው በማድረግ፣ ውጤታማ ሥራዎችን አከናውናለች::

በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች አጠናክራ በመቀጠል እያከናወነቻቸው ስላሉ ተግባራትና በተለይም ከሀገራዊ ለውጥ በኋላ በተሰሩ ሥራዎች የተመዘገቡ ውጤቶችና ስኬቶች፣ እንዲሁም ወደፊት ስለሚጠበቁ ሥራዎች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተው አቅርበናል:: መልካም የንባብ ጊዜ::

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራዊ ለውጥ ከተደረገ ወዲህ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ እንዴት ይታያል?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በዋናነት ትኩረቱ የሀገር ውስጥ ሰላምን፣ ልማትን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት:: ሀገር ውስጥ ለሚሠሩ የልማት ሥራዎቻችን ተጨማሪ ኢንቨስትመንት፣ የልማት ፋይናንስ፣ የቴክኒክ ትብብርን፣ የቴክሎጂ ሽግግር፣ ማምጣት አለበት:: ስለዚህ የሀገር ውስጥ ልማት ዲፕሎማሲያችን በውስጥ ያለውን የልማት ስትራተጂያችንን ፤ የልማት ፖሊሲያችንን የሚደግፍ መሆን አለበት::

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አንዱና ዋነኛ የትኩረት መስክ ተደርገው ከተለዩ የዲፕሎማሲ ዘርፎች መካከል ይጠቀሳል:: ሚሲዮኖቻችን፣ ዲፕሎማቶቻችን ይሄንን ሥራ ለማገዝ ዋንኛ የትኩረት መስካቸውና ተልእኮአቸው አድርገው እንዲሠሩ ይጠበቃል:: ከፖለቲካ ዲፕሎማሲ ጎን ለጎን ኃይላችንም፣ በጀታችንም፣ ሊውል የሚችለው የኢትዮጵያ ምርቶችንና ቱሪዝምን በማስተዋወቅ፤ እንዲሁም የኢንቨስትመትና የቢዝነስ ፎረሞችን በማዘጋጀት የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገር መሳብ መሆን አለበት ::

ዲፕሎማሲያችን የሀገር ውስጥ ልማትን፣ ሰላምን ከማገዝ አኳያ በውጭ የሚገኙ እድሎች ላይ መሥራት ትልቁ ግቡ ነው:: የሚሲዮኖቻችን ቅኝትም ተልእኮም ከዚህ አኳያ የተስተካከለ እንዲሆን የማድረግ፤ አብዛኛው ሥራችን ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት፤ የፖለቲካ ዲፕሎማሲም የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ማዕከል አድርጎ እንዲሠራ የማድረግ ሥራ ነው እየተሠራ ያለው::

ስለዚህ ከኢንቨስትምንት ኮሚሽን፣ ከቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስርና ከሌሎችም ተቋማት ጋር በትብብር የምንሠራቸው ሥራዎች በዋነኛነት የሀገር ውስጥ ልማት እንዲፋጠን ነው:: ንግድና ኢንቨስትመንትን ማስተዋወቅ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማዕከል በማድረግ ነው ሥራዎች የሚሠሩት::

ሀገራዊ ለውጥ ከተደረገ ወዲህ ባሉት ዓመታት፤ ኢንቨስትመንት፣ የወጪ ንግድ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲጨምር፣ የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ሥራዎች፣ በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ የልማት ሥራዎች እንዲጠናከሩ፣ ‹ኢንቨሰት ኢን ኢትዮጵያ› የሚለው ዓመታዊ የኢንቨስትመንት ፎረም እንዲካሄድ ከኢንቨስትመት ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሆን ሥራዎች እንዲሠሩ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡ ፡ የነፃ የንግድ ቀጣናዎችንም ለመቀላቀል ጥረቶች እየተደረጉ ነው::

በውጭ ፖሊሲያችን ትኩረት ተደርገው ከሚሠሩ ሥራዎች አንዱ የወጭ የንግድ ቀጣናዎችን መቀላቀል ነው:: በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጎረቤት ሀገሮች፣ ከዓለም ጋር ትስስር እንዲጨመር አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው:: የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል ለመሆን የሚያስችሉ ሥራዎችም ከድርጅቱ ጋር እየተሠራ ነው:: የአፍሪካ ነፃ ቀጣና የንግድ ድርጅት ጋር ኢትዮጵያ ተቀላቅላለች:: ሙሉ ለሙሉ ወደ ንግድ ለመግባት የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው::

የሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ ሥራዎቻችንን ከፍ ያለ እገዛ እንዲደረግ፤ አካባቢያዊ ውህደትን የሚያጠናክር ሥራም እየተሠራ ነው:: የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በዋነኝነት በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ያነጣጠረ ነው ስንል ኢንቨስትመንት፣ ንግድና ቱሪዝምን ማስተዋወቅ ቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግርን ያካተተ ሥራ ተጨማሪ የልማት ፋይናንስ በሁለትዮሽ ደረጃ የልማት ድጋፎችን ማምጣት፤ እንዲሁም በሁለትዮሽ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚሠሩ ሥራዎች የሀገር ውስጥ ልማትን የሚያግዙ መሆን አለባቸው:: የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ስንል በዋናነት ትኩረት የምናደርገው፤ ሀገር ውስጥ የሚሠሩ የልማት ሥራዎቻችን በውጭ ዲፕሎማሲ ማገዝ ነው::

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የኢንቨስትመት እንቅስቃሴው ምርጥ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከሆኑ የአፍሪካ ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ ትጠቀሳለች:: የወጭ ንግድም ቢሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ እያመጣ ነው:: አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች ቁጥር እየጨመረ ነው:: ወደ ውጭ የመላክ አቅም የሚጨምሩ የተለያዩ አቅም የሚፈጥሩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው::

ከፍተኛ በሚባሉ የኢንቨስትመንትና ንግድ ባዛሮች ላይ የመሳተፍ ብቻ ሳይሆን፣ በራስ አቅምም ዲዛይን በማድረግ በውጭ ሀገራት ባዛሮችንና ኤክስፖዎችን አዘጋጅቶ መሳተፍ ተችሏል:: በዚህ ረገድ በተለይ ሚሲዮኖቻችን ከፍተኛ ሥራ እየሠሩ ነው:: እንዲህ ያሉ ጥረቶች በዋናነት የኢትዮጵያ ምርቶች የገበያ ዕድል እንዲያገኙ፣ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆንና የሚመጣው ኢንቨስተርም ቁጥር እንዲጨምር ነው::

የኢትዮያን የኢንቨስትመንት አማራጮች በማስተዋወቅ ረገድ፣ ፎረሞች ላይ ያተኮሩ የማስተዋወቅ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ:: በተለይም ውጤት ተኮር የሆኑ ኢንቨስትመንትን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ትኩረት ይደረጋል:: አንድ ለአንድ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት የምልመላ ሥራ በጣም ውጤታማ በመሆኑ በዚህ ረገድም የመመልመል ሥራ ይሠራል:: ይሄ በቅንጅት ከተለያዩ ኤምባሲዎች ተስረቶ የሚመጣውን ወደ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በመላክ፤ በክትትልና ድጋፍ ጭምር የሚሠራ ሥራ ነው::

በንግድም እንዲሁ የግብርና ምርት፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶች፣ በጨርቃጨርቅ፣ በቆዳ አዳዲስ ገበያዎችን በመፈለግ ሥራች ይሠራሉ:: ይሄም በስፋት መከናወን ያለበት ሥራ ነው:: በተለይም የአፍሪካ ንግድ ቀጣና ውስጥ ከገባን በኋላ ወደ አፍሪካ የሚላኩ ምርቶች እንዲጨምሩ ሚሲዮኖቻችን ሰፊ ሥራ ይሠራሉ ብለን እንጠብቃለን:: በዚህ መልኩ ነው እየተንቀሳቀስን ያለነው::

**አዲስ ዘመን፡- ከሰጡን ማብራሪያ አንጻር ከየትኞቹ ሀገራት ጋር ነው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲያችን እየተሳለጠ ያለው? ወዳጅ ከማብዛት አንጻር ኢትዮጵያ እየሄደችበት ያለውን ርቀት አያይዘው ቢገልጹልን?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** ለምሳሌ ቡናን የምንልክባቸው መዳረሻዎች አሉ:: እንደ ሰሊጥ ቦለቄ ያሉ የግብርና ምርቶች፣ አበባ፣ ጨርቃጨርቅ፣ የመሳሰሉ ባህላዊ ወይንም በተለምዶ የገበያ መዳረሻዎች አሉ:: አዳዲስ ገበያዎችን መፈለግ ላይ ነው ትኩረት አድርግን እየሠራን ያለነው:: መካከለኛው ምሥራቅ፣ አውሮፓና አሜሪካን ትልቅ የገበያና ኢንቨስትመንት መዳረሻዎች ናቸው::

በዋነኛነት ግን ከፍተኛው ኢንቨስትመት ከኤዢያ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ የሚመጡ ኢንቨስትመንቶች ናቸው:: እዚህ አካባቢ ትኩረት ሰጥተን የምንሠራበት ነው:: መካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በአካባቢያዊ (ጅግራፊ) እና በባህል ቅርበት ስላለን በርካታ እድሎች ያሉበት ነው:: በነዚህ አካባቢ ሰፋ ያለ የማስተዋወቅ ሥራዎች በመሥራት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ኢንቨስትመንትን መሳብ ያስችላል::

ከህንድና ከቻይና የሚመጡ ኢንቨስተሮችንም እንዲሁ በቴክኖሎጂ ሽግግር አዳዲስ ኢንቨስተመንት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ማድረግ ይቻላል:: ለምሳሌ ቻይና ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ ስላላት አዲስ የቡና ገበያ መዳረሻ አድርገን ቡና ወደ ቻይና ሀገር ብንልክ ሰፊ የገበያ እድል እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል:: በስምምነት ደረጃም ጥሩ የሚባል ሁኔታ ተፈጥሯል::

በስጋ ምርትም አዳዲስ ገበያዎችን ለመፈለግ ጥረት እየተደረገ ነው:: እኛ መሥራት ያለብን በሀገር ውስጥ ሳይቆራረጥ አቅርቦቱን አስተማማኝ ማድረግ ነው:: ይህን ማድረግ ከቻልን፣ በጥራት ላይ ከሠራን የገበያ እድሉ ሰፊ ነው:: ስለዚህ ኢንቨስትመንት ምልመላና ንግድ ማስተዋወቅ ላይ ትኩረት አድርገን መሥራት ይኖርብናል:: ባህላዊ የገበያ መዳረሻ የምንላቸው የኢትዮጵያን ቡና እና ሌሎች የግብርና ውጤቶች በሚገዙም ሀገሮችም ቢሆን የበለጠ ገበያው እንዲሰፋ መሥራት ይጠበቃል::

ሚስዮኖችንም የተከፈቱት ለውክልና ብቻ ተብለው አይደለም:: ለኢትዮጵያ ልማት አጋዥ በሆነ መልኩ እንዲሠሩ ነው:: ሀገር ውስጥ ላለው የልማት ሥራችን ተጨማሪ የገበያ ዕድል፣ ኢንቨስትመንት፣ የንግድ እድል፣ የቱሪዝም አቅም ፣የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ መፍጠር ይኖርብናል :: ቅኝታችንም፣ ሥልጠናችንም፣ የሥራ እንቅስቃሴያችንም፣ በዚህ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል የሚል አቅጣጫ ተሰጥቶ እየተሠራበት ይገኛል::

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ተቀዛቅዞ ...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ በኋላ ከኢኮኖሚ እና ከፖለቲካ ዲፕሎማሲም በተለይም ከሁለትዮሽ ግንኙነት አንጻር የመጡ ለውጦች ምንድን ናቸው?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** ከለውጡ በኋላ የዲፕሎማሲ አካሄዳችን የሚያተኩረው፤ አጋርነት፣ ወዳጅነትና ትብብር እንዲሁም አዳዲስ ወዳጅነት ማስፋት ላይ ነው። በአንድ አካባቢ ላይ ብቻ ሙጭጭ ያለ፣ ይሄ ብቻ ወዳጄ ነው ብሎ የተቸነከረ ዲፕሎማሲ አይደለም። ይሄ ዋንኛው ሽፍት ነው። በዲፕሎማሲ፣ በውጭ ግንኙነት ሥራ ቋሚ ወዳጅ የለም። ቋሚ ጠላት የለም። ዘላቂ ጥቅም እንጂ ይባላል። ስለዚህ እኛ ወዳጅነታችንን ከሁሉም ጋር ማስፋት ይኖርብናል።

በዋንኝነትም የወዳጅነት ትኩረታችን ቅርባችን ካሉት የአፍሪካ ጎረቤት ሀገሮች ነው። ከጎረቤት ያለው የሰላምና የልማት እድል፣ ትብብር፣ ይጠቅማል። ጎረቤት እሳት ሲቃጠል፣ እኛን በቀጥታ ይጎዳናል። ስለዚህ ከጎቤቶቻችን ጋር በሰላም፣ በትብብር፣ በወዳጅነት፣ በጋራ መልማት እና መበልጸግ እንፈልጋለን። በመሠረተ ልማት ላይ የተሳሰረ ዲፕሎማሲ እንዲኖረን ነው ምንፈልገውም ለዚህ ነው። ሀገሮችም ይሄን እንዲረዱ ነው የሚደረገው። ኢትዮጵያ ልማት አመንጪ ሀገር ናት 120 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር ናት። ሰፊ የገበያ ዕድልም ያላት ናት። ሰፊ የመልማት አቅም አላት። እና በአካባቢው ያለንን ተመራጭ አጋርነት እንዲያውቁ የማድረግ ጭምር ሥራ መሥራት አለብን። ስለዚህ ኢትዮጵያ ስጋት ሳትሆን፣ የልማት፣ የእድገት ትብብር ምንጭ ፣ የእድገት፣ የንግድ አጋር ልትሆን የምትችል መሆኗን ማሳየት አለብን። ለጎረቤት ሰላም፣ ልማት የምትሠራ ሀገር፣ አልምታ በዚያ ልማት ጎረቤቶችዋም እንዲጠቀሙ የምትፈልግ ሀገር መሆኗን ማሳየት፣ ማስገንዘብ አለብን።

አንዱ የትኩረት መስካችን ጎረቤት ሀገር ላይ ማድረግ ነው። በተጨማሪ ከቆዩ ወዳጅ ሀገሮች ጋር ልማታችንና ትብብራችንን የማጠናከር፣ የማስፋት፣ ለአካባቢ መረጋጋት ልማት የምትሠራው ሥራ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ቁልፍ ሀገር እንደሆነች በማስገንዘብ ነው ሥራዎች እየተሠሩ ያሉት። በአጠቃላይ ከሀገራዊ ለውጡ በኋላ ከጎረቤት ሀገሮች እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ትብብር ላይ በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ የተጠናከረ አጋርነት በማስፋት ረገድ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ከዚህ አኳያ በተለይ በሰሜኑ ኢትዮጵያ ተካሂዶ ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ ከምእራባውያን ጋር ተቀዛቅዞ የነበረው ዲፕሎማሲያችንን የማጠናከር ሥራ ተሠርቷል። በዚህ በጣም ማለፊያ የሚባሉ ከአውሮፓ ህብረት፣ ከአሜሪካን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር፣ ማሻሻል፣ የቻልንበት ነው። ከዚህ አኳያ ውጤታማ ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በወጭ ጉዳይ ሴክረተሪ ደረጃ በኢትዮጵያ ጉብኝት ተደርጓል። እኛም በመሪ ደረጃ ጉብኝት አድርገናል። የአፍሪካ ዩኤስ ሰሚት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመገኘት በመሪ ደረጃ ሰፊ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በዚህ ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ ሰፊ ሥራ እየሠራች እንደሆነ ማስገንዘብ ተችሏል። ግንኙነታችንን ከፍ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

ከዚህ ውጭ ከምዕራብ ሀገሮችም ከጣሊያን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጀምሮ የጣሊያን መሪው እንዲሁም የፈረሳይ፣ የጀርመን፣ የጃፓን፣ የደቡብ ኮሪያ፣ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና ሌሎችም ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል። በዚህ ዲፕሎማሲውን መልሶ ማጠናከር በተሠራው ሥራ ታግደው የቆዩ የነበሩ የፋይናንስና የሠብዓዊ ድጋፎች እንዲለቀቁ መንገድ መክፍት ተችሏል። በአሜሪካን በኩል እስከ ሶስት መቶ ሰላሳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሠብዓዊ ድጋፍ እንዲጀመር ተደርጓል።

በተጨማሪም ከዓለም ባንክ ጋርም ተቋርጠው የነበሩ ግንኙነቶች ማስቀጠል ተችሏል። ከአውሮፓ ህብረት ጋርም በተመሳሳይ ግንኙነት በመፍጠር ተቋርጦ የነበረው ብድርና ሌሎችም ተግባራት እንደገና መጀመራቸው ከተሠሩት ሥራዎች ውስጥ ይጠቀሳሉ።

በተቋም ደረጃ እነዚህ በመሪ ደረጃ የተጀመሩ ሥራዎችን ተከታትሎ በማስፈጸም ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። በዚህ የለውጥ ወቅት ሊጠቀስ የሚገባው በሁለትዮሽ ግንኑነት ደረጃ ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏ ይሄም የዲፕሎማሲ ውጤት ነው። ይሄ በትልቁ መታወስ ያለበት ስኬት ነው።

የፖለቲካ ምክክር መድረኮችም በማዘጋጀት ካናዳ፣ ፖሩቹጋል፣ ሲውዘርላንድን ጨምሮ ከበርካታ ሀገራት ጋር ምክክር በማድረግ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ



> **ከጎረቤት ሀገሮች እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ትብብር ላይ በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ የተጠናከረ አጋርነት በማስፋት ረገድ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል**

በተመሳሳይ ሥራዎች ተሠርተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ በኋላ የሲፕሎማሲው አቅጣጫ ዜጋ ተኮር መሆኑ እየተገለጸ ነው ፤ ስለዚህ ጉዳይ ቢያብራሩልን?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** ለውጡ ይዟቸው ከመጣቸው ትሩፋቶች አንዱ ለዜጎች ክብር የሚሰጥ እና የዜጎቻችንን ደህንነት ላይ የሚያተኩር ዲፕሎማሲ መቀየሱ ነው። ዜጎቻችን በሚሠሩባቸው የተለያዩ ሀገራት መብታቸው ክብራቸው እንዲጠበቅ፣ በሚሄዱበት ሀገር ተጨማሪ የሥራ እድል እንዲያገኙ የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነትም ተደርጓል። ለአብነትም ኳታር፣ ሳውዲ፣ ጆርዳን ሀገራት ይጠቀሳሉ። ወደ ሀገርም መመለስ የሚፈልጉ ዜጎች መብታቸው፣ ክብራቸው ተጠብቆ እንዲመለሱ በማድረግ ረገድም ሰፊ ሥራ ተሠርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ከአምስት የኢኮኖሚ ምንጩች መካከል አንዱ ስለሆነው የቱሪዝም ኢንዱስትሪም አንስተውልናል። በዚህ ረገድ የተሠሩ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ምን ይመስላሉ**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ እምቅ አቅም እንዳላት ይታወቃል። እንደተባለውም አሁን የምንገኝበት ወቅት ዘርፉ በከፍተኛ ሁኔታ ይነቃቃል። በዚህ ረገድ ዲጂታል ዲፕሎማሲን ማጠናከር ያስፈልጋል። ዘርፉን በተለምዶ ከምናስተዋውቅበት ወጥተን ዜጎች ስለሀገራቸው ሰላም፣ ደህንነት፣ እንዲሁም በሀገራቸው ውስጥ ስላለው እምቅ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ወጥተው መመስከር፣ ማስተዋወቅ አለባቸው።

ቱሪስት ሲመጣ የሆቴልና የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጡ ይነቃቃሉ። ለወጣቶች የሥራ እድል ይፈጠራል። የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። ይሄ የሁሉም ሥራ ነው። ይሄን ግንዛቤ በመያዝ ያገባኛል የሚሉ ሁሉ ሳይቀሩ በመተባበር ለዘርፉ እድገት ጥረት ማድረግ አለባቸው። እኛ ስለሀገራችን በጎ በተናገርነው ልክ ነው ሌላውም ሊዳምጠን የሚችለው።

የምንገኝበትን ወቅት ቱሪስቶችም ይፈልጉታል። ኢትዮጵያም ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በኢኮኖሚው ተጠቃሚ የምትሆንበት ነው። ስለዚህ ሚሲዮኖቻችንም ሀገሮች የጉዞ አማካሪዎች ስላሏቸው እነርሱንም ጭምር በመከታተል የማስተዋወቅ ሥራ እንዲሠሩ እናደርጋለን። ሀገር ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ በጎ ሥራዎችም እንዲሁ ሌላው ዓለም እንዲያውቀው የማድረግ ሥራ እንሠራለን።

**አዲስ ዘመን፡-ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ሰላምና መረጋጋት ወሳኝ ናቸው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በገጠማት የውስጥ ችግር ዘርፉ ላይ ተጽእኖ መፈጠሩ አይቀርም። በዚህ ተጽእኖ ውስጥም ሆኖ በዘርፉ በተጨባጭ ምን ሥራዎች ተሠሩ?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** ኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ የተረጋጋ ሰላምና ፀጥታ እንደሚፈልግ ይታወቃል። ሰላም በእጃችን ነው ያለው። ዜጎች ሰላም ወዳድ መሆን አለባቸው። እኛ ችግራችን የልማት እጦት ነው። ያገኘነውን ገንዘብ፣ ከ ልማት ውጪ የምናጠፋ ከሆነ፣ ገንዘቡን ይዞ መጥቶ ኢትዮጵያ ማነው ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት የሚኖረው።

ስለዚህ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሰላም ዘብ መቆም አለበት። መጀመሪያ ከራሱ ጋር ሰላም መሆን መቻል አለበት። ያለውን ሰላምና ልማት ጠብቆ ማቆየት የሚችል ሕዝብ ነው መሆን ያለበት። ለሰላም ለልማት የማንከፍለው ዋጋ መኖር የለበትም። ኢንቨስትመንትን ስናስብ የሆነ አካል በየአካባቢያችን መጥቶ ሰላምን እንዲያስከብርልን መጠበቅ የለብንም። በየአካባቢያችን ለልማት፣ ለንግድ፣ ለቱሪዝም፣ ምቹ ነን ወይ የሚለውን ከታችኛው መዋቅር ጀምሮ በቅንጅት መሥራት ይኖርብናል።

በእርግጥ የሚነሱትን ስጋቶች ለመቅረፍ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ለውጦችና መሻሻሎችም እየታዩ ነው። ኢኮኖሚያችን እያደገ ነው። የልማት ሥራዎችም ተጠናክረዋል። የሰላም ግንባታ ተብለው እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። ሕዝቡም ትኩረት በነዚህ ላይ መሆን አለበት። ባለቤትም ሆኖ ለጋራ ጥቅም መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚሁ ጋር በተያያዘ አምራች ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ጉዳይ ለሥራቸው ማነቆ እንደሆነባቸው ጥያቄ ያነሳሉ። እዚህ ላይ የርስዎ ምላሽ ምንድ ነው?**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** የውጭ ምንዛሪ እጥረት እየለማን ስለመሆኑ ማሳያ ነው ብዬ ነው የማስበው። እዚህ ሀገር ብዙ ዶላር እንበላለን ማለት ነው። ልማት ባይኖር ኖሮ የልማት ፍላጎታችን ብዙ አይሆንም ነበር። በሀገራችን ከዚህ ቀደም ያልነበረ ፍላጎት ነው የዶላር አቅርቦት ጥያቄ። ብዙ ዶላር የሚፈልግ የልማት ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል።

ልማት በሌለበት ሀገር የዶላር ጥያቄ የለም። እኛ ለልማቱ የሚውል የሥራ መሣሪያ ወይንም ማሽነሪዎች ከውጭ እናስገባለን። የልማት ኢንዱስትሪዎቹም እንዲሁ ከውጭ ግብዓት ይፈልጋሉ። ለግብርናው ሥራ የሚውል ማዳበሪያ እንዲሁም ነዳጅ ከውጭ ነው በግዥ ወደ ሀገር የሚገቡት። የዶላር ጥያቄ የኢኮኖሚ እድገት የፈጠረው አንዱ ፍላጎት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

አቅርቦቱን ይበልጥ ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ግን ይታመናል። ማሻሻሉ የሚመጣው ደግሞ የወጪ ንግድ ወይንም ኤክስፖርትን በመጨመር ነው። ወደ ውጭ የሚላኩ ነገሮችን በመጨመር የውጭ ምንዛሪን ማሳደግ ተገቢ ነው። ዜጎች ለሀገራቸው ቀናኢ መሆን መቻል አለባቸው። ለሕጋዊነት ተገዥ መሆን አለባቸው። በኤሊሲ፣ በጥቁር ገበያ፣ በሕገወጥ የሚወጣ ነገርን በሙሉ መግታት መቻል አለብን።

ሕገወጥነትን ማስቀረት ስንችል፣ ኢንቨስትመንትን ስንስብ፣ የዶላር አቅርቦት እጥረት በጊዜ ሂደት እየቀነሰ ይሄዳል። አሁን ባለው ሁኔታ የዶላር አቅርቦት ጥያቄን ሙሉ ለሙሉ ማሟላት ወይንም ለጥያቄው ምላሽ መስጠት ባይቻልም ልማቱ መቆም የለበትም። ልማታችን በፍጥነት እየሄደ ነው። ሰፊ የመሠረተ ልማቶችም በመከናወን ላይ ይገኛሉ። በዚህ መንገድ መረዳቱ የተሻለ ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ከተነሱ ሃሳቦች ውጭ ቀሩ የሚሏቸው ሃሳቦች ካሉ ቢገልጹልን**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** የዲፕሎማሲ ሥራችን፤ በአንድ ተቋም ብቻ የሚሠራ ካለመሆኑ ጋር በተያያዘ፤ ሲቲዝን ጆርናሊዝም፣ ዲፕሎማሲ፣ ዲጂታል ዲፕሎማሲ፣ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ስለዚህ በዲጂታል ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ሥራ ከሚዲያው ጀምሮ ይጠበቃል። ስለሀገራችን በጎ ሥራ እኛ ሳንናገር ሌላው ሊናገር አይችልም።

ስለሀገራችን በጎነትም ሆነ ኢንቨስትመንትን ስለ መሳብ ሥራው በአንድ ተቋም ብቻ የሚሠራ አይደለም። ለሀገራዊ፣ ብሄራዊ ጥቅሞች ሁሉም ዜጋ ያገባዋል። ይመለከተዋል። በቅንጅት መሥራት የሁላችንም ተልእኮ መሆን አለበት።

በተለይ ደግሞ ተቋማት የተናበበ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ መሆን አለባቸው። ኢትዮጵያ ትልቅ አቅም አላት። ይህ አቅም እንዲወጣ ሁሉም ዜጋ ከተረባረበ የልማት ትብብርን መጨመር፣ ንግድን ማስፋፋት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንት እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ የሁሉም ተቋማት ቅንጅታዊ ሥራ በጣም ወሳኝ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አምባሳደር ስነበረን ቆይታ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።**

**አምባሳደር ምስጋኑ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሁሉን ያማከለው የባህል አልባሳት ኪራይ

**ሰሚራ በርሀ**

ሰዎች በእለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ምንም እንኳን ፋሽን ተከታይ ባይሆኑም በሥራ ቦታ የሚለብሱት፣ ለመዝናናት ብለው የለዩት ፣ ለልዩ ፕሮግራሞቻቸው ብቻ ያስቀመጡት እና እንደየሚሄዱበት ፕሮግራምና እንደሚገኙበት ቦታ የሚጠቀሙበትን ልብስ ይለያሉ:: ከቁም ሳጥናቸው ውስጥ ለዚህ ብለው ለይተው ያኖሩት ልብስም ሊኖራቸውም ይችላል::

አልያም ደግሞ ልብሳቸው ወቅቱን እና ፋሽኑን ያልጠበቀ ሲሆንባቸው፣ ከሌሎች ወዳጆቻቸው ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ልብሶችን መልበስ ሲፈልጉ ደግሞ አዲስ ልብስ ለመግዛት ወይንም ለማሠራት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ::

በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ሰዎች ከሚሄዱበት ፕሮግራም ይልቅ የሚለብሱት ልብስ፣ በተጓዙበት ቦታ ይዘው ከሚሄዱት ስጦታ በላይ ለብሰው የሚገኙት ልብስ ያስጨንቃቸው ጀምሯል:: ለእዚህ አንደኛው ምክንያት በተለየ ፕሮግራም ላይ ለየት ብሎ መታየት ሲሆን፣ ሌላኛው ግን ልብሶቹ የሚሠሩበት ዋጋ ከኑሯቸው እና ከበጀታቸው ጋር የማይመጣጠን እየሆነ መምጣቱ ነው::

ለዚህ መፍትሄ ይሆን ዘንድም ሰዎች ወጣ ያሉ አልባሳት ማለትም ለየት ላለ ፕሮግራም ብቻ የሚለበሱ ልብሶችን ለመግዛት ወይም ለማሠራት ለአንድ ቀን ብቻ ብለው ያልተገባ ወጪን ከሚያመጡ ይልቅ እነዚህን ልብሶች አዘጋጅተው በኪራይ መልክ የሚያቀርቡትን እያማተሩ መጥተዋል::

ትግስት ትባላለች:: /ሙሉ ስሟ እንዲጠቀስ አልፈለገችም/ በሽሮሜዳ የባህል አልባሳት ውስጥ የተለያዩ ወቅታቸውን የጠበቁና ለዓይን የሚማርኩ የባህል አልባሳትን ለደንበኞቿ ታቀርባለች:: ትግስት ከቤተሰቦቿ ጋር በመሆን የምትሰራው የባህል አልባሳትን ሰርቶ በኪራይ መልክ የማቅረብ ሥራ ዘጠኝ ዓመት ገደማ አስቆጥሯል:: በእነ ትእግስት መደብርም ከተለያዩ ተመሳሳይ የባህል አልባሳት ባሻገር በርከት ያሉ የሠርግ ልብሶች እንዲሁ ይገኛሉ::



መነሻ ሃሳቡ በየጊዜው የሚሠሩ የባህል አልባሳት እንደሚፈለጉበት ፕሮግራም እና እንደሚፈጁት ግብዓት ዋጋቸው ከፍ ያለ መሆኑ ነው:: እነ ትእግስት ለእዚህ መፍትሄ ያሉት የአልባሳት ኪራይ ነው:: ይህ አገልግሎ አቅሙ የማይፈቅድ ሰው የወደደውንና የመረጠውን ልብስ በኪራይ መልክ ወስዶ በቅናሽ ዋጋ ተጠቅሞ መመለስ የሚያስችል ነው፤ «ሰዎች ይህን ማድረጋቸው አዳዲስ ፋሽኖችንም ለመከተል ያስችላቸዋል::» በማለት ተመራጭ የሆነበትን ምክንያት ትናገራለች::

በኪራይ የሚቀርቡት ልብሶች ሌላ ተመራጭ የሚያደርጋቸው ምክንያት እንዳለም ትእግስት ታብራራለች:: ይህ አማራጭ ሰዎች በህብረት ሆነው አንድ አይነት ልብስ ለአንድ ቀን ፕሮግራም ብለው ከሚያሠሩ፣ ተሠርተው የተዘጋጁ ልብሶችን በሚፈልጉት መልኩ መርጠው በመከራየት በሚፈልጉት ፕሮግራም ላይ አምረውና ደምቀው መዋል ያስችላቸዋል ትላለች::

እነዚህ የባህል አልባሳትን የሚያከራዩ ሰዎችም በአሁኑ ወቅት እየበረከቱ መጥተዋል:: በአብዛኛው ከግል ይልቅ በቡድን ሆነው ለመከራየት የሚመጡ ተጠቃሚዎች እየተበራከቱ ናቸው::

ለሠርግ አልያም በባህላችን ከሰርግ በኋላ በሚደረገው የመልስ ፕሮግራምም በባህል አልባሳት ደምቀው መታየት የሚፈልጉ ሙሽሮችም አሉ:: ሙሽሮቹ የሚፈልጓቸውን አልባሳት በሙሉ የሙሽራውና የሙሽሪትን ካባ ፣ የሚዜዎችንም አልባሳት ጨምሮ በሚፈልጉት መልኩ ከጊዜው ፋሽን ጋር በማጣመር በአንድ ቦታ ማግኘት እንደሚቻልም በሱቁ ውስጥ ተመልክተናል::

«ለሰርግ በሚደረጉ ፕሮግራሞች ላይ የሚዜዎች ቁጥር እስከ ስድስት ይደርሳል፤ አጃቢዎችም ከ10 በላይ እየሆኑ ስለመጡ እኛም አንድ አይነት ልብሶችን በርከት አድርገን እናዘጋጃለን » የምትለው ትእግስት፣ በቁጥር በዛ ብለው ለሚመጡ ደንበኞች የሚሆኑ አልባሳትን አስቀድሞ ከ 16 እስከ 20 የሚደርሱ አንድ አይነት ልብሶችን ሠርተው እንደሚያቀርቡ ገልጻለች::

ከሰርግ ወቅት ባለፈም ለጥምቀትና ለተለያዩ በዓላት ፣ ለቤተሰብ ፕሮግራሞች ሰዎች አንድ አይነት ልብስ ፈልገው ወደሱቃቸው እንደሚሄዱም ትናገራለች::

በኪራይ የሚቀርቡ አልባሳት ተመራጭ የመሆናቸው ዋነኛው ምክንያት ለማሠራት ከሚወጣው ወጪ እጅግ ባነሰ ዋጋ ሰዎች ለሚፈልጓቸው ቀናት ያህል ወስደው ተጠቅመው መመለስ መቻላቸው ነው ትላለች:: በቡድን ሆነ በግል ለመከራየት የሚመጡ ደንበኞች ከአንድ ሺ 500 ብር ጀምሮ እስከ አምስት ሺህ ብር የሚደርሱ የተለያዩ የባህል አልባሳት እንዳሉም ጠቁማለች::

አልባሳቱ ተዘጋጅተው ለኪራይ በሚቀርቡበት ጊዜ የታጠበ እና ያልታጠበ ተብለው እንደሚለዩ፣ የተለበሰ እና ያልተለበሰ በማለት እንደሚለዩም ሰምተናል:: ልዩነቱም የባህል አልባሳት በአብዛኛው በእጅ በጥንቃቄ የሚሠሩ በመሆናቸው አንድ ጊዜ ተለብሰው ከታጠቡ በኋላ በጥቂቱ ሳቢነታቸው የሚቀንስ በመሆኑ እንደሆነም ትእግስት ገለጻ፤ አንዴ ከተለበሱ በኋላ ዋጋቸው እየቀነሰ እንደሚሄድ ትናገራለች ::

ሌላኛዋ የተለያዩ የሀገር ባህል ቀሚሶችን በማከራየት ሥራ የተሠማራችው ብስራት በቀለ ናት:: ብስራት ከቤተሰቦቿ ጋር በመሆን ነው የምትሰራው:: « በበዓለ እንጦጦ ኪዳነምህረት የሀገር ባህል ልብስና የሚዜዎች ልብስ ማከራያ » ቤት ውስጥ ደንበኞችን ስታስተናግድ ነው ያገኘናት ::

«ከዚህ በፊት የምንሠራው ትእዛዞችን እየተቀበልን መሸጥና ተሠርተው የተዘጋጁ ልብሶችን ማቅረብ ነበር» የምትለው ብስራት፣ ሱቃቸው የሚገኝበት ቦታ ከዋናው መንገድ ገባ ያለ በመሆኑ ከስራው ወቅታዊነት ጋር ተያይዞ የሚሠሯቸውን የባህል አልባሳት ከመሸጥ ወደ ማከራየት መምጣታቸውን ትናገራለች::

ብስራት በኪራይ የምታቀርባቸው ልብሶች ለተለያዩ ፕሮግራሞች የሚፈልጉ እና በቡድን ለሚመጡ ሰዎች እና ለሙሽሮች የሚሆኑ ናቸው:: የሙሽራውና የሙሽሪትን ልብስና ካባን ጨምሮ ከ ሶስት ሺህ 500 ብር ጀምሮ እስከ ስምንት ሺህ ብር ድረስ በተለያየ አማራጭ በኪራይ እንደሚቀርቡም አመልክታለች::

ብስራት ልብሶቹን የምታቀርባቸው ጊዜውን በሚመጥን ሳቢነቱን እና ባህሉን በጠበቀ መልኩ ነው:: ለሽማኔ ተሰጥተው፣ ጠላፊ እጅ ገብተው የሚዘጋጁና ብዙ ብር የወጣባቸው መሆናቸውን ጠቅሳ፣ ለመከራየት የሚመጡ ሰዎች የአከራይ እና ተከራይ ውል እንዲገቡ እንደሚደረግም ትናገራለች::

«ውላችን ላይ መውሰጃ ቀን እና መመለሻ ቀን ይቀመጣል:: ለኪራይ ከሚከፍሉት ብር ሌላ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያና የልብሱን ዋጋ ባይተካም ደንበኞች ልብሱን ሲመልሱ የሚመለስ ገንዘብን እንደማስያዣ እንቀበላለን» ስትል ትገልጻለች :: የልብስ ኪራይ ሥራ ገበያው የሰፋ የሚሆነው በሰርግ ወቅት መሆኑን ጠቅሳ፣ ከደንበኞች ጋር ያለው ተቀባይነት ጥሩ መሆኑንም ትገልጻለች ::

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ኢትዮጵያን ለዓለም የሚያሳዩት ገና እና ጥምቀት

**ዋሰልኝ አየለ**

«ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች ሀገር ናት» የሚለው አገላለጽ በጣም ስለተደጋገመ ምናልባትም አሰልቺ ይመስል ይሆናል:: ምናልባትም ለአንዳንዶች ራሳችንን ለማካበድ የምንጠቀመው ወይም የተለመደ ተረት ተረት ይመስላቸው ይሆናል::

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች መሆኗን ለማሳየት ግን የሳይንስ ጥናትም ሆነ የፈላስፋ ጥቅስ መጥቀስ አያስፈልገውም:: በየወቅቱ በዓለም መገናኛ ብዙኃን የምናየውና የምንሰማው ሀቅ ነው:: የውጭ ሀገራትን የማየት ዕድል ያገኙ ደግሞ በዓይናቸው ያዩት ነው::

የሥልጣኔ ማማ ላይ ያሉ ሀገራት በከፍተኛ ሙቀት ወይም በከፍተኛ ብርድ ይጠቃሉ፤ በአየር ንብረት ምክንያት የበርካታ ሰዎች ሕይወት ያልፋል:: ተሽከርካሪዎቻቸው ሥራ እስከማቆም የደረሱባቸውን አጋጣሚዎች አይተናል:: ለዚያውም እነዚህ የበለጸጉ ሀገራት አለ የሚባለውን የሙቀትም ሆነ የቅዝቃዜ መከላከያ የሚጠቀሙ ናቸው::

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ የ13 ወር የፀሐይ ፀጋ ያላት ሀገር ናት:: አልፎ አልፎ ሙቀትና ቅዝቃዜ ቢኖርም የሰው ሕይወት የሚቀጥፍና ተሽከርካሪን ሥራ የሚያስቆም ግን የለንም::

በዚህ አየር ንብረት ምክንያት ብዙ አይነት የዕፅዋትና አዝርዕት አይነቶች አሉን:: በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የእንስሳት አይነቶች አሉን:: አስገራሚ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ቦታዎች አሉን::

ታዲያ ይህን ድንቅ ተፈጥሮ፣ ውብ ባህልና ትውፊት ለዓለም የምናስተዋውቀው መቼ ነው? ምንም እንኳን ሀገርን ለማስተዋወቅ የጊዜ ገደብ ባይኖረውም የታህሳስና ጥር ወራት ግን የበለጠ ምቹ ናቸው:: ምክንያቱም የገና እና የጥምቀት በዓላት አሉን:: ሁለቱም የዓለም ሕዝብ የሚመለከታቸው ናቸው:: ገና የዓለም ሀብት በሆነው ላልይበላ ይከበራል:: ጥምቀት ደግሞ አከባበሩ በራሱ የዓለም ሀብት ሆኗል::

እነዚህ በዓላት የሚከበሩት ከሚከበሩበት ቀን ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት እና የሚከበሩበት ቀን ካለፈም በኋላ ነው:: ለምሳሌ ለገና የመጡ የውጭ ሀገራት እንግዶች የመጡት ቀደም ብለው ነው:: አሁንም ይኖራሉ:: የፊታችን ቅዳሜ ጥር 11 ለሚከበረው የጥምቀት በዓልም እንግዶች ከወዲሁ መግባት ይጀምራሉ::

እንግዲህ አገራችንን የምናስታዋውቃት በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው:: ብዙዎቻችን ለውጭ ዜጎች ሀገርን ማስተዋወቅ የአስጎብኚዎች ሚና ብቻ ይመስለናል:: በሀገሩ ጉዳይ ማንም አስጎብኚ ነው:: ለውጭ ሀገራት ዜጎች ተገቢውን መረጃ መስጠት የሁላችንም ኃላፊነት ነው::

ይህን ለማለት የተገደድኩበት ምክንያት በብዙ ቦታዎች የምታዘበው ነገር ስላለ ነው:: ባረፍንበት ቦታ፣ በገባንበት ካፌ፣ በምንጓዝበት ተሽከርካሪ ውስጥ፤ እንዲሁም፣ በዓላቱ በሚከበሩባቸው ቦታዎች ላይ የውጭ ዜጎችን እናያለን:: ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ለእነዚህ የውጭ ዜጎች ያላቸው አቀባበልና መረጃ አሰጣጥ ልክ አይደለም::

እርግጥ ነው የቋንቋ ገደብ ይኖራል፤ ችግሩ ግን የቋንቋ ብቻ ሳይሆን የአመለካከትም ጭምር መሆኑ ነው:: አንዳንዱ ልክ እንደ ኩራት በማየት ለነጭ አልለማመጥም አይነት ምልክት ያሳያል:: እንግዳን መንከባከብ ፍርሃት ወይም ባርነት ሳይሆን ትህትና ነው::

አዎ! በቅኝ ያልተገዛን፣ ወራሪን አሳፍረን የመለስን፣ የራሳችን ማንነት ያለን ነን:: ይህን የምናሳየው ግን እንግዳ ሆኖ በመጣ አካል ላይ አይደለም:: እዚህ ላይ ከሁለት ዓመት በፊት የተከሰተ የአንድ ግለሰብ ገጠመኝ ልጥቀስ::

ግለሰቡ ከአንዲት ሴት ጓደኛው ጋር ካፌ ውስጥ ቁጭ ብሏል:: ወደ መታጠቢያ ክፍል እንደሄደ አራት የውጭ ዜጎች ወደ ካፌው ገቡ:: ካፌው ውስጥ ያሉ ቦታዎች ተይዘው፤ አራት ሰው መያዝ የሚችል ያለው እነዚህ ሴትና ወንድ የተቀመጡበት ቦታ ብቻ ነው::

የካፌው ባለቤት ይሁን ሥራ አስኪያጅ በትህትና ወደ ልጅቷ ሄዶ «እናንተ ሁለት ስለሆናችሁ እዚያች ጋ ብትቀመጡ» ብሎ ለሁለት ሰዎች የሚሆነውን ቦታ እየጠቆመ በትህትና ነገራት:: ልጅቷም በትህትና እሺ ብላ ተነስታ ሁለት ሰው ብቻ ወደሚይዘው ቦታ ሄደች::

ልጁ ከመታጠቢያ ክፍል ሲመለስ ቦታ ቀይራለች:: «ምነው?» ሲላት የሆነውን ነገረችው:: በፊት የተቀመጡበት ቦታ ላይ የውጭ ዜጎችን ሲያይ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ:: እንደ ዓድዋ ያሉ የታሪክ ድሎችን መዘርዘር ጀመረ:: «ኸረ ባክህ ይሄ ከእርሱ ጋር አይገናኝም!» ቢባል ሊሰማ አልቻለም:: በመጨረሻም ካፌውን ለቆ ሄደ::

እስኪ ይህን ነገር በቅንነት እንየው! እንግዶቹ አራት ናቸው፡፡ እነዚህኞቹ ደግሞ ሁለት ናቸው:: ታዲያ ቦታ ቢቀይሯቸው ምን ችግር አለው? በዚያ ላይ የውጭ ዜጎች አይደሉም ተነሱልን ያሉት፤ የካፌው ባለቤት ነው በትህትና የጠየቃቸው:: በትህትና መጠየቁን ደግሞ ያዙኝ ልቀቁኝ ያለው ልጅ ራሱ አምኗል::

እንዲህ አይነት ስሜቶችን እንደ ሀገር ፍቅር አላያቸውም፡፡ እንዲያውም ሀገርን እንዴት ማስተዋወቅ እንዳለብን አለማወቃችንን ነው የሚያሳየው:: አዎ! ሀገርን ለማስተዋወቅ ባሪያ እና አጎብዳጅ መሆን የለብንም፣ ለፈረንጅ መስገድ የለብንም፤ ዳሩ ግን አግባብ ባልሆነ ሁኔታ መፎከር ደግሞ ኋላቀርነትን እንጂ ሥልጣኔን ወይም ኩሩነትን አያሳይም::

ሀገርን ማስተዋወቅ ምርትና አገልግሎትን እንደማስተዋወቅ ነው:: የሰዎች አዕምሮ ውስጥ መሥራት ነው:: ማስተዋወቅ ደግሞ አወንታዊ ጎኖችን ለይቶ ማጉላት ማለት ነው:: በለጸጉ በሚባሉ ሀገራትም እያየነው ያለነው ይህንኑ ነው:: በፊልሞቻቸውና በባህላቸው ውስጣችን ገብተዋል::

በፊልሞቿና ባህሏ የምንወዳት ሕንድ የድሃ ድሃ የሚባሉ ሕዝቦች ያሉባት ናት:: በየዘጋቢ ፊልሞች እንደምናየው እጅግ አስደንጋጭ የሆነ የችግር ኑሮ የሚኖሩ አሏት፤ ዳሩ ግን በሰራችው ራስን የማስተዋወቅ ሥራ ህንድ የምትታወቀው በዚህ አይደለም::

የዓለም ልዕለ ኃያል የምትባለው አሜሪካ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የጦር መሣሪያ የሚይዙ ኋላ ቀሮች ያሉባት ናት:: ባለፈው ዓመት እንኳን አንድ የስድስት ዓመት ሕጻን መምህሩን በሽጉጥ አቁስሏል:: ይህ በተደጋጋሚ በየጊዜው የሚሰማ ነው:: እንዲያውም የቀድሞው ፕሬዚዳንቷ ዶናልድ ትራምፕ መምህራኑን አስታጥቃለሁ ሲሉ ነበር:: ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አሜሪካ የምትታወቀው የሥልጣኔ ጣሪያ በመሆኗ ነው:: የምትታወቀው ሌሎች ሀገራትን ኋላ ቀር እያለች በመውቀስ ነው:: ይህ ሁሉ የሆነው በጎ በጎ ነገሮቿ ላይ ጠንክራ በመሥራቷ ነው::

እኛ ኢትዮጵያውያን ግን እንዲህ ተፈጥሮ አድሎን፣ ሰው ሠራሽ ችግሮቻችን ግን ኋላቀር አድርገውናል:: ስለዚህ ከእነዚህ ችግሮች እንላቀቅ:: ሀገራችንን በበጎ እናስተዋውቅ:: ለዚህ ደግሞ እንደ ገና፣ ጥምቀትና መስቀል የመሳሰሉ በዓላት ምቹ ናቸው::

ሀገርን ማስተዋወቅ ሲባል የግድ እነዚህን ቀናት ብቻ መጠበቅ አይደለም:: ቀደም ሲል እንዳልኩት በየትኛውም አጋጣሚ ለምናገኛቸው እንግዶች ተገቢውን መረጃ መስጠት ነው::

የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ አንድ ልብ ያልኩት ነገር አለ:: የውጭ ዜጋ የሆኑ መምህራን ገና ወደ ክፍል የገቡ ቀን የመጀመሪያ ሥራቸው ስለሀገራቸው መናገር ነው:: የሀገራቸው ምርት የሆኑ ነገሮችን ከቦርሳ እያወጡ ይሰጡናል:: በተለይም የአውሮፓ ሀገራትና የህንድ ዜጎች ይህን ነገር በሚገባ ይጠቀሙታል::

ሁሉም ሰው ለሀገሩ አስጎብኚ ነውና በእንዲህ አይነት አጋጣሚዎች ሀገራችንን እናስተዋውቅ!

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ ጉዞ - ከግድብ እስከ ወደብ

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያ ፈተና የማያጣት ሀገር ነች:: ከቤት አስከ ጎረቤት የምትፈተን ጎዞዋ ሁሉ ከሜዳነት ይልቅ ዳገትና ቁልቁለት የሚበዛበት ነው:: ሆኖም ጽኑ በሆኑ ሕዝቦቿና ቆራጥ በሆኑ መሪዎቿ በመታገዝ እሾህና አሜኬላውን እያወስወገደች፤ ለጠላቶቿ የነብር አራስ እየሆነች አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን አስከብራ ዛሬ ላይ ደርሳለች::

የኢትዮጵያ አፈጣጠር አስገራሚ ነው:: በዓለም ላይ በሚባሉ የዓባይ ተፋሰስና የቀይ ባህር አዋሳኝ መሃል የምተገኝ፤ ከዳሉል እስከ ራስ ዳሸን የዘለቀ ሙቀትና ቅዝቃዜን በአንድነት የታቀፈች፤ የሰው ልጅ መገኛና የተለያዩ የተፈጥሮ ጸጋዎች መዳረሻ ነች::

ከመቀበል ይልቅ መስጠትን የምትመርጥ፤ ከመንጠቅ ይልቅ መቸርን የምትሻ ቸር ሀገር ነች:: ለዚሁ መሳያ ደግሞ በዓለም ላይ አንድም የተፈጥሮ ሀብት ከጎረቤቷ የማትወስድና ይልቁንም ለሁሉም ጎረቤቶቿ ውሃን የምትሰጥ ድንቅ ሀገር ነች::

የመስጠት እናት የሆነችው ይህች ሀገር የእራሷን ሀብት እንኳን በአግባቡ እንዳትጠቀም ችግሮች ሲፈትኗት ኖረዋል፤ ዛሬም እየፈተኗት ነው:: “የዓባይ ልጅ ውሃ ጠማው” እንዲሉ በደጇ ከሚፈሰው ውሃ እፍኝ እንዳትጠጣ ተከልክላ ኖራለች:: ለብዙዎች ከሚተርፈው የባህር በሯ ተገፍትራ በሯን ዘግታ ለመቆየት ተገዳ ቆይታለች::

ሆኖም ለፈተናና የማትንበረከከው ሀገር የታሰረችበትን ገመድ በጣጥሳ ፤ የተከረቸመባትን በር በርግዳ ፤ እሾህና አሜኬላውን አስወግዳ ጠላቶቿን ማሳፈር ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል:: የዘመናት ቁጭት የነበረው የዓባይ ውሃ ተገድቦ ለኢትዮጵያም ለምስራቅ አፍሪካም ብርሃን መሆን ጀምሯል::

ኢትዮጵያ የዓባይ ንዑስ ተፋሰስ የሆነው ጥቁር ዓባይ ምንጭ ነች:: እስከ 86 በመቶ የሚደርሰውም የናይል ወንዝ ውሃ የሚነጨውም ከዚቹ ሀገር ነው:: ይህ የውሃ ድርሻዋም እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ባለሙሉ መብትና ባለብዙ ተጽዕኖ አሳራፊ ሀገር እንድትሆን አስችሏታል::

ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ያላትን መብትና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጣች መጥታለች:: በተቃራኒው በቅኝ ግዛት አሳሪው ውሎች ምክንያት ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ከማልማት እጇን አጣጥፋ ለመቀመጥ የተገደደችበት እውነታ ዛሬም ድረስ ለአንዳንዶች የመደራደሪያ አጀንዳ እንደሆነ ነው::

በታሪካዊ እና ተፈጥሮአዊ መብቶች ላይ ተመሥርተው በታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ከሚቀርቡ የመብት ክርክሮች መለስ ዓባይን አስመልክቶ እስከአሁን ያለውን ሕጋዊ ሁኔታ በዋናነት የሚወስኑ ሁለት ሰነዶች ናቸው ፣ የመጀመሪያው በቅኝ ግዛት ዘመን እ.ኤ.አ ግንቦት 7 ቀን 1929 በታላቋ ብሪታኒያና በግብፅ መካከል የተደረገው ስምምነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሰላሳ ዓመት ቆይታ በኋላ ከነጻነት ወዲህ እ.ኤ.አ ሕዳር 8 ቀን 1959 በሱዳንና ግብፅ መካከል የተፈረሙ ስምምነቶች ናቸው::

እነዚህ ሁለት ስምምነቶች በሚፈረሙበት ወቅት እንግሊዝ ከላይኛው ተፋሰስ ሀገራት ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ኡጋንዳን፣ እና ኬንያን በመወከል ግዴታ ከመግባትዋ ውጪ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎቹ የተፋሰሱ ሀገራት ተካፋይ አልነበሩም:: በተለይም ኢትዮጵያ በወቅቱ ነፃ ሀገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በስምምነቱ ተካፋይ መሆን ቢገባትም በሂደቱ በጋራ መብትዋን እንድትወስን ምንም አይነት ጥያቄ ሳይቀርብላት ቀርቷል::

በ1929 እና 1959 በተደረጉት ስምምነቶች መሠረት ግብፅ በዓባይ ላይ የፍሰቱን ባለቤትነት መብት ስትጎናፀፍና በተጠቃሚነት ረገድም ከ55 ቢሊዮን ኪዩብ በላይ ድርሻ እንዲኖራት ሱዳንም 18 ቢሊዮን ኪዩቢክ የውሃ መጠን ድርሻ እንዲኖራት ተደርጓል። ከ86 በመቶ በላይ የውሃው ባለቤት የሆነች ኢትዮጵያ ግን ቅንጣት ታክል የውሃ ድርሻ እንዲኖራት አልተደረገም::

እነዚህ ሁለቱ ስምምነቶች እስከዛሬም ድረስ በህዳሴ ግድብ ላይ በሚደረጉ ውይይቶች እንደማጣቀሻ እየቀረቡ ግብጾች በማደናገርያነት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ:: ኢትዮጵያንም በእነዚህ አሳሪ ሕጎች እንድትገዛና የበይ ተመልካች ሆና እንድትቀር ዛሬም ድረስ በመወትወት ላይ ይገኛሉ:: አልፎ ተርፎም የዓባይ ውሃ ከሀገርና አህጉር አልፎ ዓለም አቀፍ መወያያ እንዲሆን በማድረግ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ በብዙ ጥረዋል::

ኢትዮጵያም የጋራ ተጠቃሚነትን በማስቀደም ከግብጽ እና ሱዳን ጋር ተከታታይነት ያላቸውን ድርድሮች በማድረግና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ አካሄድን በመከተል ዛሬ ላይ ደርሳለች:: እግረ መንገዷንም የህዳሴ ግድብ ግንባታን ከ94 በመቶ በላይ በማድረስ መጪውን ብሩህ ተስፋ በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች:: የግድቡ መገባደድም የኢትዮጵያዊነት የአይበገሬነት ማሳያ ሃውልት ተደርጎ የሚወደስ ነው::

ዛሬ ደግሞ ተራው የቀይ ባህር ይመስላል:: ቀይ ባሕር ባአፍሪቃና በእስያ መሃል የሚገኝ ረጅም ባሕረ ሰላጤ ነው። የቀይ ባሕር አካባቢ ከፍተኛ የዓለም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግበት፤ በርካታ መርከቦች በስዊዝ ካናልና በባብኤል ማንዴብ ሸርጦች የሚተላለፉበት፤ በርካታ ሀገራት ትኩረት ሰጥተውት ፀጥታው የተረጋጋ እንዲሆን የሚጓጉለት፤ በርካታ ያካባቢው ሀገራት በባሕር መተላለፊያው ላይ ጉልህ የሆነ ተጽእኖ ሊያደርጉበት የሚፈልጉ መተላለፊያ፤ አንዳንዶቹ ሀገራት ደግሞ ይባስ ብሎም የአካባቢው ሁነኛ አዛዦች ለመሆን የሚፈልጉት ዓለም አቀፋዊ መተላለፊያ ነው::

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባህር ላይ ይዞታ የነበራትና ቀይ ባህርንም ስታዝበት የኖረች ሀገር ነች:: 1 ሺ 800 ኪሎሜትር የሚረዝመውን የቀይ ባህር ይዞታ በቁጥጥሯ ስር ያኖረችና ለወጪና ገቢ እቃዎች ሁለት ወደቦች የምታስተዳድር ሀገር ነበረች:: ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ውጪ ቀይባህርንም ከኢትዮጵያ ውጭ ማሰብ አይቻልም ነበር::

የኢትዮጵያን ማደግ በማይፈልጉ ኃይላት ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትወገድ ተደርጓል:: ለዘመናትም ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ምንም ድርሻ እንዳልነበራት ሆን ተብሎ በተሰራጨው ትርክት ኢትዮጵያና ቀይ ባህር ለሶስት አስትርት ዓመታት ተቆጥረው ቆይተዋል::

> **ኢትዮጵያ**
> **በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት 16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው**

ቀይ ባህር ከሕዝቡ ልብ ውስጥ ማውጣት ባይቻልም ስለቀይ ባህር ማሰብና ማውራት እንደ ሀጢያት ሲቆጠር ቆይቷል:: ባለፉት 30 ዓመታት ስለወደብና ባህር በር ማውራትም ሆነ የኢትዮጵያን የባለቤትነት መብት መጠይቅ እንደነውር ከማስቆጠሩም በላይ ጸብ አጫሪ አስብሎም በነገረኛነት ያስፈርጅ ነበር::

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከሥነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል::

ለበርካታ መሠረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ 1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል::

በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትዮጵያ ሚና አሽቆልቁሏል:: ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ በዓለም እጅግ ተፈላጊ ከሆኑትና የሃያላን ሀገራትንም ቀልብ የሚስብ በመሆኑ እድገቷን የማይፈልጉ አካላት በተቀነባበረ ሴራ ከቀይ ባህር እስኪያርቋት ድረስ ገናና እና በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ ሆና ቆይታለች::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት 16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ 126 ሚሊዮን ደርሷል:: በአጠቃላይም በኢትዮጵያ የሚኖረው ሕዝብ የባህር በር የሌላቸውን ሀገራት ሕዝብ 1/3ኛውን ይሸፍናል::

ይሄንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ የባህር በርና ወደብ የተነፈገ ሀገር የለም:: ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያ በባህር በር የተከበበች ሀገር ነች:: ከላይ እንደጠቀስኩት በሴራ እና በተሳሳተ ትርክት ከቀይ ባህር እንድትርቅ ከመደረጓ በስተቀር በአፈጣጠሯ ለቀይ ባህር የቀረበ ነው:: በሶስተኛ ደረጃ በታሪክም በቀይ ባህር ላይ ለዘመናት የበላይ ሆና መቆየቷን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ያሏት ሀገር ነች::

ኢትዮጵያ በግፍ ከይዞታዋ እንድትነቀል ከመደረጓ ውጪ ባለቤትነቷን የሚከለክላት አንዳችም ዓለም አቀፍ ሕግ የለም:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባህር እንድትወገድ የተደረገበት አካሄድ ምንም አይነት ሕጋዊ መሠረት የሌለው ነው :: ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትወገድና ወደብ አልባ እንድትሆን የተደረገው በ1900፤ 1902 እና 1908 ከቅኝ ገዚዎች በተደረጉ ውሎች አማካኝነት ነው:: እነዚህ ውሎች ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት መመስረቻ ቻርተር ሕጋዊነታቸውን አጥተዋል::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲቋቋም ካወጣቸው ድንጋጌዎች አንዱ ሀገራት የቅኝ ግዛት ውሎችን የመቀበል ግዴታ እንደሌለባቸው የሚደነግገው አንቀጽ አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ሀገር ካለመሆኗም ባሻገር በቅኝ ገዢዎች የተረቀቁትን የ 1900፤ 1902 እና 1908 ውሎችን የመቀበል ግዴታም የለባትም::

ኢትዮጵያ የባህር በር እንድታጣ ከሆነችባቸው ውሎች መካከል የቅኝ ግዛት ውሎች ተጠቃሾች ናቸው:: ከአጼ ምኒልክ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዚዎች ጋር ያደረገቻቸው ስምምነቶች የባህር በሯን አሳጥተዋታል:: የቅኝ ግዛት ስምምነቶች በባህሪያቸው ቅኝ ሲገዙ የነበሩ ኃይሎች በአስገዳጅ መልኩ ቀኝ ገዢዎች ላይ የፈጸሙት ደባ ነው::

ይህንን እውነታ / ውል ከማለት ይልቅ በጉልበተኛና በደካማ መካከል የተፈጸመ አስገዳጅ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል:: እነዚህ ውሎች የቅኝ ገዢዎችን እንጂ የተገዢዎችን ሙሉ ፈቃደኝነት የያዙ አይደሉም:: ከዚህ የተነሳም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የ 1900፤ የ 1902 እና የ 1908 ውሎች ገዢ ውሎች አይደሉም፤ ተፈጻሚነትም አይኖራቸውም::

እነዚህ ውሎች በተባበሩት መንግሥታት ማቋቋሚያ ቻርተር ላይም ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው በግልጽ ተደንግጓል:: እነዚህንና ሌሎች አጋዥ ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመንተራስ ኢትዮጵያ ዛሬ ፊቷን ወደ ባህር በር አድርጋለች:: በኢትዮጵያ አዲስ የመንግሥት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሠራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባህር በር ጥያቄ ነው::

መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባህር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል:: ለ27 ዓመታት ያህል ፈርሶ የቆየውን የባህር ኃይል እንደገና በማደራጀት ኢትዮጵያ እንደገና የባህር ኃይል እንዲኖራት አድርጓል::

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባህር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል:: ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል ቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ሰሞኑን ከሶማሊ ላንድ ጋር የባህር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል ::

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ በር የሚከፍት ነው:: ቀጣናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል::

በአጠቃላይ በየዘመናቱ በርካታ ችግሮችን እየተጋፈጠች በአይበገሬነት እየተጓዘች ያለችው ኢትዮጵያ ዛሬም አዲስ ታሪክ በመጻፍ ላይ ትገኛለች:: ከግድብ እስከ ወደብ በአሸናፊነት ሰገነት ላይ ወጥታ ደምቃ በመታየት ላይ ትገኛለች:: ሆኖም እነዚህ ስኬቶች የበለጠ እንዲጎሉና ዘላቂነት እንዲኖራቸው ሰላም ወሳኝ ጉዳይ ነው::

ሀገር በጀመረችው ግስጋሴ መቀጠል የምትችለው ሰላም ሲኖር ነው:: እዚህም እዚያም ያሉ ግጭቶች ሊቆሙ ይገባል:: የኢትዮጵያን እድገት የማይሹ ወገኖች ክፍተቶቻችንን ተጠቅመው የጀመርነውን የባህር በር የማግኘት መብት እንዳያሰናክሉብን አንድነታችን ሊጠናከር ይገባል:: ይህ ሲሆን የበርካታ ግድቦችና ወደቦች ባለቤት ከመሆን የሚያግደን ነገር አይኖርም ::